አንድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 120 ታኅሣሥ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

# አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች የተጋሩበት የገና ማዕድ

ጌትነት ተስፋማርያም

ዘመድ እያለኝ ዘመድ እንደሌለው ሆኜ ኖሬያለሁ፤ ቤተሰብ ያልኳቸው ፊታቸውን ቢያዞሩብኝም የእርጅናዬን ዘመን ቃሊቲ በሚገኘው የአረጋውያን ማዕከል እያሳለፍኩ ነው። አሁን ደግሞ የገናን በዓል ከአገሪቷ ትልቁ የስልጣን እርከን ላይ ከሚገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ጋር አብሬ አሳልፌያለሁ። በዚህም በብቸኝነት የተጎዳው ውስጤ ታድሷል ከልቤም ደስ ብሎኛል የሚሉት ወይዘሮ እታገኝ ኃይለማርያም ናቸው።

ዕድሜያቸው በግምት ስልሳዎቹን እንደሚጠጋ የሚናገሩት ወይዘሮ እታገኝ፤ አካል ጉዳተኛ በመሆናቸው ያለ ዌልቸር እገዛ እንደማይንቀሳቀሱ አስረድተዋል።

ይሁንና ካለሁበት ቃሊቲ በትራንስፖርት አምጥተው በአንድነት ፓርክ ውስጥ የእየሱስ ክርስቶስን ልደት በዓል እንዳከብር አድርገውኛል። ለእኔ በጎውን እንዳደረጉ ለእነሱም መልካሙ ሁሉ ይግጠማቸው ሲሉ ማዕድ ላጋሯቸው ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

አረጋውያንና ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



## “አፋሮች ከኢትዮጵያ አልፈው የቀጣናው ትስስር እንዲጠናከር የሚሰሩ ሕዝቦች ናቸው”

- መሃሪ መአሾ (ሻለቃ)
የቀድሞ የትግራይና የወሎ ክፍለ አገሮች ምክትል አስተዳዳሪ

ገጽ 5

# የሰላም ስምምነቱን ለማጽናት ሚዲያው አዳዲስ የመረጃ ምንጮች ላይ ማተኮር አለበት

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የተፈጠረውን ሰላም ዘላቂ ለማድረግ መገናኛ ብዙሃን በጦርነት ወቅት የአባባሽ ንግግር ተሳታፊ የነበሩትን አካላት በመተው አዳዲስ ምንጮች ላይ ማተኮር እንዳለባቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኮሙዩኒኬሽንና የጋዜጠኝነት መምህርና ተመራማሪ ዶክተር አብዲሳ ዘርአይ ገለጹ።

ዶክተር አብዲሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በጦርነት ወቅት በብዙ ንግግር ላይ ሲሳተፉ፣ በግራም በቀኝም ጦርነቱን ሲያጋግሉ የነበሩ ሰዎች አሁን በመገናኛ ብዙሃን የሰላም ተንታኝ ሆነው መቅረብ የለባቸውም። የተፈጠረው ሰላም እንዲዘልቅ እነዚህ ሰዎች ከአውዱ ዞር ማለት አለባቸው።

ለጊዜው ዘወር ማለት ያለባቸው የቤተሰቡን አባል ያጣ ሰው እነርሱን ሲመለከት ስሜቱ ሊነካ ስለሚችል ነው ያሉት ዶክተር አብዲሳ፣ ተንታኝ ተብለው የሚቀርቡ ሰዎች በፊት አጥፉ፣ ግደሉ በማለት ሲያነሳሱ፣ ስለሰላም የሚያወራውን እንደ ወንጀለኛ ሲቆጥሩ የነበሩ



ዶክተር አብዲሳ ዘርአይ

መሆናቸውን አስታውሰዋል።

እነዚህ ሰዎች የሰላም ተንታኝ ሆነው የሰላም አስፈላጊነትን እንዲናገሩ ማድረግ ተቋሙን ታማኝነት እንደሚያሳጣ አመልክተው፤ እነዚህን ሰዎች ወደ ብዙሃን መገናኛ በማምጣት እንደ ምንጭነት ከመጠቀም መቆጠብ ያስፈልጋል። አዳዲስ ፊቶችን እና ተአማኒነት ያላቸው

የሰላም ስምምነቱን ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል











# በጥር ወር ለሚጀመረው የተፋሰስ ልማት አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል

ስምስም መንግሥቱ

አዲስ አበባ፡- ከጥር ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለሚከናወነው የተፋሰስ ልማት ሥራ አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።አምስት ሺህ የማህበረሰብ ተፋሰሶችን ለማልማት የአምስት ዓመት ፕሮጀክት ተቀርጾ ከሁለት ዓመት በፊት ወደ ትግበራ መግባቱንም አስታውቋል።

በግብርና ሚኒስቴር የተፋሰስ ልማት ዴስክ ኃላፊ አቶ ዮሴፍ አሰፋ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤አሁን ወቅቱ የአፈርና ጥበቃ ሥራ የሚከናወንበት ጊዜ ነው። በፌዴራልና በክልል ደረጃ ሥልጠናዎች በመስጠት

በጥር ወር ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል






## በመጪዎቹ 20 ቀናት ከ10 ሺህ በላይ ዜጎች ወደ አገራቸው ሲመለሱ ነው

ገጽ 2

# በመጪዎቹ 20 ቀናት ከ10 ሺህ በላይ ዜጎች ወደ አገራቸው ሲመለሱ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በመጪዎቹ 20 ቀናት ውስጥ ከ10 ሺህ በላይ ዜጎችን ወደ አገራቸው ለመመለስ እየተሰራ መሆኑን የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ።

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የህገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ደረጀ ተግይበሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ መንግስት በህግ ወጥ መልኩ ከአገር ተሰደው በተለያዩ አገራት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ዜጎችን ወደ አገራቸው የመመለስ ስራ እየሰራ ነው፤ በዚህም በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዙሮች ከ94 ሺህ በላይ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው መመለስ ተችሏል። በመጪዎቹ 20 ቀናት ውስጥም ከ10ሺ በላይ ዜጎችን ወደ አገራቸው ለመመለስ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

በመጀመሪያ ዙር ወደ አገራቸው ከመጡት 71 ሺህ ዜጎች መካከል አድራሻቸው በትክክል የተለዩትንና መረጃቸው ከክልሎች በደረሰን መሠረት 19 ሺህዎቹን በመለየት ወደ ስራ እንዲገቡ የመስሪያ ቦታ የተመቻቸላቸውና ለእያንዳንዳቸው መንቀሳቀሻ ገንዘብ 18ሺህ500 ብር ድጋፍ እንደተደረገላቸው ገልፀዋል።

ከስደት ለተመለሱ ዜጎች ሁለት ዓይነት ድጋፍ የሚያገኙ መሆኑን ገልጸው፤ እስከ አምስት ወር ጊዜ ውስጥ የኑሮ መደጎሚያና ከዚያ በኋላ ደግሞ ቋሚ የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ የሚያስችል ድጋፍ መሆኑን ተናግረዋል።

ወደ ሀገራቸው በሙሉ ጤንነት የሚመጡ ዜጎች እንዳሉ ሁሉ የአካል ጉዳት ደርሶባቸውና የሥነልቦና ችግር አጋጥሟቸው የሚመጡ እንዳሉ ገልጸው፤ እነዚህ ዜጎች የህክምና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ወደ ሆስፒታሎች፤ እንዲሁም የሥነልቦና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ደግሞ የስነ ልቦና ባለሙያዎች ድጋፍ እንዲያገኙ እየተደረገ ነው ብለዋል።

ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸው የሚመጡ ዜጎችን የተለያዩ አጋር ድርጅቶችን ትብብር እየጠየቅን ወደ መጠለያ ውስጥ ገብተው ክትትልና ድጋፍ እንዲያገኙ እየተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል።

እንደ አቶ ደረጀ ገለፃ፤ ከስደት ተመላሾች ቀደም ብለው በሚኖሩበት ክልል የፀጥታ ችግር በመኖሩ መረጃቸውን መሰብሰብና ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ አስቸጋሪ ሆኗል። ለአብነትም በአማራ ክልል ብቻ በነበረው ጦርነት ምክንያት በመጀመሪያ ዙር ከተመለሱ 29ሺህ ዜጎች መካከል 15ሺህ የሚደርሱ ብቻ ነው አድራሻቸው የተገኘው። እንዲሁም በኦሮሚያ ክልልም በጸጥታ ምክንያት በርካታዎቹ አድራሻቸው ሊገኝ ባለመቻሉ ድጋፍ ለመስጠት አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሯል።

እስከ አሁን በሁለቱም ዙር ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ 94ሺህ ዜጎች 14 በመቶ ሴቶች ሲሆኑ 85 ወንዶች መሆናቸውን አቶ ደረጀ ጠቁመው፤ ተመላሽ ዜጎቹ የሚኖሩበትን አካባቢ መሠረት ባደረጉ የስራ መስኮች እንደሚሰማሩ ተደርጓል ብለዋል።

ከስደት ተመላሽ ለሆኑ ዜጎች ዘላቂ የስራ ዕድል ለመፍጠር መንግስት ከሚያደርገው ጥረት ጎን ለጎንም ህብረተሰቡና ግብረሰናይ ድርጅቶች ዜጎች ዳግም ለስደት እንዳይጋለጡ የተለያዩ የሥራ እድሎችን በመፍጠርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በመስጠት ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ወጣቶች አስቸጋሪና ፈታኝ ከሆነው ህገወጥ ስደት በመቆጠብ በሀገራቸው ሰርተው መለወጥ በሚችሉባቸው የስራ መስኮች በመሰማራት የተሻለ ኑሮን ለመምራት ጥረት እንዲያደርጉም መክረዋል።

# የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን 5ሚሊዮን ሊትር የፓልም ዘይት እያሠራጨ ይገኛል

**መስከረም ሰይፉ**




አዲስ አበባ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ግዢ ለመፈጸም ውል ከተፈረመበት 21 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሊትር ዘይት ውስጥ 5 ሚሊዮን ሊትር የፓልም ዘይት እያሰራጨ መሆኑን አስታውቋል።

የኮርፖሬሽኑ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ እቴነሽ ደገፋ እንዳሉት፤በአገር ውስጥ የሚታየው የዘይት ምርት ዋጋ ንረትና አቅርቦት እጥረት ችግርን ለመቅረፍ በጅቡቲ ከሚገኘው ጎልደን አፍሪካ ኩባንያ ከ43 ሚሊዮን በላይ ሊትር የፓልም የምግብ ዘይት ግዢ ለመፈጸም የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽንና የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብአቶች ልማት ድርጅቶች መፈራረማቸው ይታወቃል። በዚህም የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን በአጠቃላይ ውል ከተፈራረመበት 21 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሊትር የዘይት ምርት 5 ሚሊዮን ሊትሩ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱንና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እያሰራጨ ይገኛል።

ከታህሳስ 21 ቀን 2015 ጀምሮ ባካሄደው የመጀመሪያ ዙር የምርት ሥርጭት ከ2 ሚሊዮን 389 ሺ በ በላይ ሊትር ዘይት መሰራጨቱን ገልጸዋል።

ዘይቱ በኮርፖሬሽኑ የምርት ማከፋፈያዎች በኩል እየተሰራጨ መሆኑን አመልክተው፤ በአሁኑ ጊዜ በባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ጋምቤላ፣ ጅማ፣ ድሬዳዋ እና አዲስ አበባ ከተሞች ተደራሽ እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

የዘይት ምርቱ መንግሥት ባወጣው የዋጋ ተመን መሠረት በሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትና በተፈቀደላቸው አቅራቢዎች አማካኝነት ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በተላለፈው ኮታ መሰረት ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እየቀረበ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

የዋጋ ተመኑ በአዲስ አበባ ባለ 3 ሊትር 314 ብር ፣ባለ 5 ሊትር 510 ብር እንዲሁም ባለ ባለ 20 ሊትሩ የፓልም ዘይት በ 2003 ብር እየተሸጠ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽንና የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብአቶች ልማት ድርጅት የግዢ ውሉን በ69 ሚሊዮን 894 ሺህ 440 የአሜሪካን ዶላር መፈራረማቸው ይታወቃል። የምግብ ዘይት ዋጋን ለማረጋጋት ታስቦ የተፈጸመው የምግብ ዘይቱ ግዢ ክፍያ በአንድ ዓመት ውስጥ የሚፈጸም መሆን ኮርፖሬሽኑ አስታውቋል።

ኮርፖሬሽኑ ውል የሚፈጸምበት ቀሪው ዘይት በተከታታይ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት የሚሰራጭ ይሆናል ብሏል።

# በግብርና ሜካናይዜሽን ፕሮግራም 89 የግብርና መሳሪያዎች ተገዝተው ቀርበዋል

**ስምስም መንግሥቱ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የግብርና ሜካናይዜሽን ፕሮግራም መተግበር ከጀመረበት በተለይም ካለፉት ሁለት አመታት ወዲህ ወደ 13 ሚሊዮን ዩሮ ተመድቦ 89 ያህል የተለያዩ የግብርና ሜካናይዜሽን መሣሪያዎች ተገዝተው መቅረባቸውን የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው እንደገለጹት፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት ወደ 13 ሚሊዮን ዩሮ ተመድቦ 89 ያህል የተለያዩ የግብርና መሣሪያዎች ተገዝተው ቀርበዋል። አሁንም የግዥ ሂደቱም ቀጥሏል። ጥቅም ላይ በዋሉት የእርሻ ትራክተሮች፣አጭደው በሚወቁ ማሽኖች(ኮምባይነሮች) አማካኝነት እየተከናወነ ያለው የእርሻ ስራም ለግብርናው መዘመን አስተዋጽኦ በማበርከት ክፍተቶችን መቅረፍ እንደተቻለ ባንኩ ማረጋገጥ ችሏል።

የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ለማቅረብ ፍላጎት ያላቸው አቅራቢዎች ቁጥርም መጨመሩን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ፕሮግራሙ ከተተገበረበት ጊዜ ጀምሮ 530 የግብርና መሳሪያዎች የግዥ ጥያቄዎች ለባንኩ መቅረባቸውን አመልክተዋል። የቀረቡት የግዥ ጥያቄዎችም በገንዘብ ወደ 82 ሚሊየን ዩሮ የሚያወጡ መሆኑን ገልጸዋል። ከእነዚህ ውስጥም 13 ሚሊዮን ዩሮ የጀርመን መንግሥት ባንኩ ደግሞ ወደ ሁለት ሚሊየን ዩሮ ማውጣታቸውንና ቀሪውን ለመሙላት ሥራዎች እንደሚጠበቁ አስረድተዋል። እየተከናወኑ ባሉ ሥራዎችም ተስፋ ሰጪ ነገሮች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

ከፍተኛውን የግብርና ሥራ የሚያከናውኑት በአነስተኛ አርሶ አደሮች ደረጃ የሚጠቀሱ መሆናቸውን የጠቆሙት ዶክተር ዮሐንስ፤አርሶአደሮቹ ከቦታቸው ሳይፈናቀሉ ባሉበት እንዲለውጡ ወይንም ትራንስፎርም እንዲያደርጉ ካስፈለገ አንዱና ዋናው መንገድ የግብርና ሜካናይዜሽን ማስፋፋት እንደሆነ ገልጸዋል።

በተለይም በኩታ ገጠም የግብርና ዘዴ የተጀመረውን እንቅስቃሴ በሜካናይዜሽን መደገፍ እንደሚቻል የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ የተጀመረው የግብርና ሜካናይዜሽን በብዙ መንገድ እየጠቀመ መሆኑንም ጠቅሰዋል። በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ የዋሉት ትራክተሮች 12ሺ ብቻ እንደነበሩና ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ግን በሺዎች የሚቆጠሩ ትራክተሮች ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን አመልክተዋል። መሻሻሎች ቢኖሩም በቂ እንዳልሆኑና የበለጠ መሰራት እንዳለበት ገልጸዋል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከልማት አጋሮች ጋር በመሆን ሰፊ ሥራ ለመሥራት እየተዘጋጀ መሆኑንም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የጀርመን ኤምባሲ የልማት ትብብር ዋና ፀሐፊ ቤንጃሚን ተድላ ሃከር በበኩላቸው እንዳሉት፤ የጀርመንና ኢትዮጵያ የቆየ የልማት ትብብር እንዳላቸውና የግብርናውን ዘርፍ በመደገፍም የቆየ ተሞክሮ መኖሩን አመልክተዋል።የልማት እድገት እንዲመዘገብም በግብርና ሜካናይዜሽን ሊዝ ፋይናንስ ፕሮግራም በመሳተፍ ትብብሩን ማሳየቱንም አመልክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓላት ደምቀው የሚከበሩትም ሆነ በደስታ የሚታለፉት ሰላም ሲኖር ብቻ ነው!

የትኛውም ሀይማኖት የሚያስተምረው የአንደበትን ፍቅር አይደለም። በድርጊት የሚታይ ፤ በስራ የሚተረጎመውን ሰላም ነው። መተሳሰብ፣ መዋደድ፣ መከባበርን የሚገልጹት ቃላት አይደሉም ፤ ተግባር ነው። በተግባር መረዳዳት ነው። ላጣ ለነጣው በማካፈል ፤ ከተረፈን ላይ ሳይሆን ካለን ላይ ቆርሶ ማጉረስ ነው። ካለው ላይ አከፍሎ መስጠት ነው። ዓመታዊ በዓላትን አብረን ተደስተን በጋራ መሳለፍ መቻልን ነው። የምንፈልገውን ነገር ለማድረግም በሃገር ላይ ሰላም እና አንድነት ያስፈልጋል።

ሰላም የጥይት ድምጽ አለመስማት ብቻ አይደለም። መተሳሰብ፣ መረዳዳት፣ ለሌሎች ወገኖቻችንም እኛን የሚያስደስተን ነገር እንዲደረግላቸው ማድረግ ነው። በሌላው መልኩ ደግሞ በራሳችን ላይ እንዲደርስብን የማንፈልገውን ነገር ሌላውም ላይ እንዳይደርስበት ማድረግ ነው። ይሄ ለሁሉም ሰው የውስጥን ሰላም የሚፈጥር ነው። የሁሉም እምነት ተከታዮች አስተምህሮ ነው። መከባበር ፤ መቻቻል፣ ችግሮችን በንግግር መፍታትና ይቅር ባይነትም የሰላም መገለጫ ናቸው። ስለዚህ ሁላችንም መስራት ያለብን ለዚህ ዓይነቱ ተግባር ነው።

ሰላም በህይወት ስንኖር ልናጣቸው ከማይገቡ ነገሮች የመጀመሪያው ነው። እንኳን ለሰው ልጆች ቀርቶ ለእንስሳትና ለእጽዋቱ ጭምር ሰላም አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ ነው። ሰላም ሲኖር በዓላትም ደምቀው ይከበራሉ። አንተ ትብስ አንቺ ብሎ በጋራ መብላት መጠጣቱ፣ ሲቸገሩ መረዳዳቱ ፤ የታመመን መጠየቁ፣ ያዘነን ማስተዛዘኑ ሁሉ ይኖራል። በተቃራኒው ሰላም ሲጠፋ ሜዳው ሁሉ ገደል ይሆናል። ነገን አርቆ ማለም ይቀራል ፤ በተስፋ ላይ ተስፋ እንቆርጣለን። ሁሉም ነገር ችግር ብቻ ሆኖ ደስታ ከአጠገብ ይርቃል። ሰውነት ልረፍ ቢል እንኳን ጣፋጭ እንቅልፍ አይገኝም። ስለዚህ ሁልጊዜም ስለሰላም መዘመር ያስፈልጋል። የተገኘን ሰላም ጠብቆ ማቆየት ይገባል። የሰላም ዋጋው ውድ ሲገኝም በጥንቃቄ የሚያዝ መሆን አለበት።

ሰላም በሌለበት ሀገር የሚመጣ ባለሀብት ፤ የሚመጣ ቱሪስት፣ የሚካሄድ ንግድና ኢንቨስትመንት ሁሉ አይኖርም። ወጥቶ መግባት አይቻልም። ሰላም ከሌለ ኢኮኖሚው ይጎዳል፤ ከውጪ ወደ ውስጥ ፤ ከውስጥ ወደ ውጪ የሚገባ የሚወጣም አይኖርም።ይሄም በኑሮ ላይ ከሚያስከትለው የኢኮኖሚ ጫና በተጨማሪ የስነልቦና ጉዳቱ የከፋ ይሆናል። በአጠቃላይ ጤናም ይታወካል። ሰላም ሲኖር ዓመታዊ በዓላትም በደስታና በተድላ ፤ ጣፍጠውና ደምቀው ይከበራሉ። እያንዳንዱ ዜጋ ውስጣዊ ደስታ ይፈጥራል። ውስጣዊ ደስታ ደግሞ በሽታን ያርቃል፤ እድሜን ያረዝማል። ስለዚህ ሰላምን አጠብቆ መሻት ይገባል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በሀገራችን ተፈጥሮ የነበረው የሰላም መደፍረስ ለመላው ሕዝብ ስጋትን የፈጠረ፣ ደስታን ያራቀ፣ ፍርሀትና አለመተማመን ያነገሰ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። በዚህም ብዙ ዜጎች ከህይወት መጥፋት እስከ ንብረት መውደም ያሉ አስከፊ ጉዳቶችን አስተናግደዋል። ጦርነቱ በሃገር ኢኮኖሚ ላይ የፈጠረው እንዲሁም በማህበራዊ ህይወት ላይ ያሳደረው ተጽዕኖም ቀላል አልነበረም። የስነልቦና ጉዳቱም ከህሊና ቶሎ የሚጠፋ አይደለም። ይሁን እንጂ አሁን በመንግስትና በሕወሓት መካከል የተፈጠረው የሰላም ስምምነት ለሀገራችን እፎይታን ሰጥቷል። መላው ሕዝብም በዚህ ደስ ተሰኝቷል። ዓመታዊ በዓል በደስታና በመተሳሰብ ማክበር ተችሏል።

ባለፉት ዓመታት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በትግራይ፣ በአፋርና በአማራ ክልሎች ከሰላም መደፍረስ ጋር ተያይዞ በዓላት በዓል ሳይመስሉ በትካዜና በጭንቀት ማለፋቸውን እናስታውሳለን ። ዛሬ ያንን አስከፊ ያለፈውን ጊዜ በምልሰት በማስታወስ የዛሬውን ሰላም በማመስገን ማክበር ተችሏል። ስለዚህ ለነገው ሰላም መጠንከር የበኩላችንን ማድረግ ይጠበቅብናል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ የጦርነት ቀጣና በነበሩ አካባቢዎች ነዋሪዎች ከማንምና ከምንም በላይ የሰላምን ናፍቆት አይተውታል። የጦርነትን አስከፊነትም ተረድተውታል። ስለዚህ ሰላም በህይወት ስንኖር ልናጣው ከማይገቡ ነገሮች መካከል የመጀመሪያው መሆኑን መረዳት ይገባል። ሰላምን በዋጋ መተመን በወርቅና ብር መግዛት አይቻልም። ሰላምን በጥንቃቄ መያዝ ያለብን የነገአችን ተስፋ ጭምር በመሆኑ ነው። ስለሆነም ሁሌም ከሰላም ጎን ልንቆምና ስለሰላም ልንዘምር ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# በዲፕሎማሲ መስክ የተገኘውን ድል ለማስቀጠል

(አቤል ገ/ኪዳን)

የፈረንጆቹ አዲስ አመት ሰሞኑን ተከብሯል።መቼም አዲስ አመት ሀገሩ ቢለያይም ወጉ አንድ ነውና ባለ አዲስ አመቶቹ ሀገራትም የየራሳቸውን አዲስ እቅድ ያቅዳሉ።በአዲሱ አመት ሊጓዙበት የሚፈልጉትን መንገድም ከአሁኑ ያስተዋውቃሉ። ታዲያ እኛ ምን አገባን የሚል ሰው ሊኖር ይችላል። የምንኖረው ሉላዊ በሆነች አለም ውስጥ ነውና የእነሱ እቅድ እኛ ላይ የሚኖረው ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ተጽእኖ ቀላል የማይባል በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ ማየት ተገቢ ነው ።

እንደሚታወቀው አሁን ያለው የአለም ስርአት ለምእራባውያኑ እንዲያመች ተደርጎ የተቀረጸ ነው።እኛ በዚህ ወቅታዊ የአለም ስርአት ውስጥ ተሳታፊ እንጂ የጨዋታውን ህግ የምናበጅ ሀገር አይደለንም።ስለዚህም እነሱ በቀጣዩ አመት ጨዋታውን እንዴት ሊጫወቱ እንዳሰቡ ሲናገሩ ልብ ብሎ መስማት ውዴታ ሳይሆን ግዴታችን ጭምር ነው።

ለመሆኑ በቀጣዩ አመት የአለም ፈተናዎች ምንድን ናቸው ተባለ? የአሜሪካ የትኩረት አቅጣጫ ወዴት ነው? የአውሮፓ ህብረትስ? የሩሲያስ? የሌላውስ? ....።አሁን ያለው የዩክሬን ጦርንትን በተመለከተ ምን አይነት አቅጣጫ እንደሚከተሉ ሩሲያስ ሆነ ምእራባውያኑ ምን አሉ? የቻይና እና የታይዋን ጉዳይስ? የነዳጅ ዋጋ በአዲሱ አመት ወዴት ይሄዳል?።

አሁን ያለው ኢኮኖሚያዊ መንገጫገጭ በአዲሱ አመት ይጠበቃል? ወረርሽኝስ? አሜረካ በየትኛው አለም አቀፍ ጉዳይ ላይ የፖሊሲ ለውጥ ልታደርግ ትችላለች? አይ ኤም ኤፍ ስለ ቀጣዩ አመት የሀገራት የኢኮኖሚ ሁኔታ ምን ተነበየ? የትኛው ምርት በአዲሱ አመት ተፈላጊ ይሆናል? የትኛውስ ምርት ዋጋ ያጣል? ወዘተ...። እነዚህ ሁሉ እኛን ሊያሳስቡን እና ልንዘጋጅባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው።

ባለፈው አመት በዲፕሎማሲው ዘርፍ ብዙ ትግል የገጠምንበት አመት ነበር።በትግራዩ ጦርነት እና በህዳሴ ግድብ ጉዳይ ብዙ ጫናዎችን አስተናግደናል። ደህና በሚባል መልኩ መክተናል ማለትም ይቻላል። ነገር ግን የአምናው ድል ለዘንድሮ ብዙም የሚፈይደው ነገር የለም። ቢበዛ የሞራል ስንቅ ቢሆን ነው።ከዚያ ውጭ ምእራባውያኑ በአዲሱ አመት በአዲስ መልክ ታጥቀው ነው የሚመጡት።ምናልባት የአምናውን ጫና ላያስቀጥሉ ይችሉ ይሆናል።ነገር ግን አዲስ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት እንደሚኖራቸው መጠራጠር አያስፈልግም።ስለዚህ ቆፍጠን ብሎ መጠበቅ ግድ ነው።

ከሁኔታዎች እንደምንረዳው አሜሪካ ብዙም አዳዲስ ለውጦች የምታስተናግድ አይሆንም።ከወራት በፊት ያካሄዱት የኮንግረስ እና ሴኔት ምርጫ ዴሞክራቶች ሴኔቱን ይዘው እንደሚቀጥሉ የሚያሳይ ሆኗል።ስለዚህም ለቀጣይ ሁለት አመታት በአሜሪካ በኩል ብዙም የአቋምም ሆነ የሹማምንት ለውጥ የማይታይበት ነው የሚሆነው። አሜሪካውያኑ ዘንድሮ ይዘው የከረሙትን አቋም በአዲሱም አመት ይዘው የሚቀጥሉ ይሆናል ማለት ነው።

ከዚህ በመነሳት እንዴት ነው ዘንድሮስ ከአንቶኒ ብሊንከን ፤ ሳማንታ ፓወር ፤ ጄክ ሱሊቫን ፤ ሊንዳ ቶማስ ግሪንፊል እና መሰሎቻቸው ጋር አብረን ልንዘልቅ የምንችለው ? በየትኛውስ ጉዳይ ላይ ዘንድሮ ጠንካራ ፍጥጫ ይገጥመናል? የሚለውን በትክክል መተንበይ እና መዘጋጀት ይገባናል።

በአውሮፓ ህብረት በኩልም ነገሮች በአብዛኛው ተመሳሳይ ቅርጽ ሊኖራቸው ይችላል።ከሰላም ስምምነቱ መፈረም በኋላ ነገሮች የመሻሻል አዝማሚያ ቢኖራቸውም ቅሉ አሁንም ቢሆን ብዙ የቤት ስራዎች በዚያ በኩል ይቀሩናል።እየተደረገብን ያለው ኢኮኖሚያዊ ጫና እንዲቀንስ እና የታገዱ እንቅስቃሴዎች እንዲቀጥሉ ማድረግ ቅደሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።መንግስት በርካታ አዎንታዊ እርምጃ እየተራመደ ባለበት በዚህ ወቅት ከዚያኛውም ወገን ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ ሳይሆን ተግባራዊ በጎ እርምጃ እንዲኖር መግፋት ያስፈልጋል።

በአዲሱ አመት በሩሲያ ዩክሬን ጦርነት ዙሪያ እስካሁን የያዝነውን አቋም እንዴት እናስቀጥላለን? ወዳጆችን ሩሲያን ሳናስከፋ ሰላም እንዲሰፍን እንዴት ማድረግ እንችላለን? የሚለው ዋነኛ ሀሳብ ይሆናል። ይህ ጦርነት በእጅ አዙር ብዙ ጉዳት አስከትሎብናል ስለዚህም ሰላም መምጣቱ ቅድሚያ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ይህን በልእለ ሀያላን መሀከል ባለ ፍልሚያ መሀል እንዴት የሀገራችንን ጥቅም ማስከበር እንችላለን የሚለው ጉዳይ ጥንቃቄ ይፈልጋል።

ምእራባውያኑ ኢትዮጵያ በዚህ ጦርነት እነሱ የደገፉትን እንድትደግፍ የሚያደርጉትን ጥረት ማጠናከራቸው አይቀርም።ስለዚህም በአዲሱ አመት ይህን ጫና ተቋቁሞ በተለይ ሞስኮው በጸጥታው ምክር ቤት እያደረገችልን ያለውን ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ማስቀጠል ወሳኝ ይሆናል።በቻይናም በኩል አዲስ የተሾሙት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሀገራችን ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲያጠናክሩ ፤ ቤጂንግም የነበራትን የልማት አጋርነት ሚና እንድታጠናክር ማበረታታት ትልቅ ስራ ይጠይቃል።

በአፍሪካ ጉዳይም ፓን አፍሪካኒዝምን ማጠናከር ፤ ከጎረቤቶቻችን ጋር ያለውን ውስብስብ ግንኙነትም በተቻለ መጠን ቅርጽ ማስያዝ ወሳኝ ጉዳይ ነው።ዛሬ ላይ ሀያላኑ ሀገራችንን የሚያጠቁት ጎረቤቶቻችንን እንደ ማኮብኮቢያ በመጠቀም በመሆኑ ጎረቤቶቻችንን እንዴት እንደምንይዝ ማወቅ አስፈላጊ ነው።እንደሚታወቀው ብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገራት የምእራቡን የቀን አቆጣጠር የሚጠቀሙ ሲሆን ከምእራባውያኑ በተለየ በየጊዜው የስርአትም ሆነ የፖሊሲ ለውጥ የሚፈጠር በመሆኑ ከየትኛው የአፍሪካ ክፍል ምን አይነት ፖለቲካዊ ነፋስ እንጠብቅ የሚለውን ማወቅ የእኛ የቤት ስራ ይሆናል።

ሲጠናቀቅ ይህ የፈረንጆቹ አዲስ አመት ለእኛ የበጀት አመት አጋማሹ ላይ የሚከበር በመሆኑ ያለፉትን 6 ወራት የዲፕሎማሲ ስራችንን አፈጻጸም ገምግመን የእነሱንም የአዲስ አመት እቅድ አይተን ማስተካከያ ለማድረግ እድል የሚሰጥ ነው።ስለዚህም ይህን አጋጣሚ መጠቀም እና ለቀጣይ 12 ወራት የአለም የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ነፋስ አቅጣጫን መገምገም አለብን። ወቅቱ ዲፕሎማሲያዊ መዝረክረክ ብዙ ዋጋ የሚያስከፍልበት ዲፕሎማሲያዊ ቅልጥፍና ደግሞ ብዙ ስኬት የሚያመጣበት ነው። ስለዚህ እንቀላጠፍ። ድል ከፊታችን ነው።

# “አፋሮች ከኢትዮጵያ አልፈው የቀጣናው ትስስር እንዲጠናከር የሚሰሩ ሕዝቦች ናቸው”

*- መሃሪ መአሾ (ሻለቃ)*
*የቀድሞ የትግራይና የወሎ ክፍል አገሮች ምክትል አስተዳዳሪ*

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- አፋሮች ከኢትዮጵያ አንድነት አልፈው የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ትስስር እንዲጠናከር አበክረው የሚሰሩ ሕዝቦች ናቸው ሲሉ የቀድሞ የትግራይ ተቀዳሚና የወሎ ክፍለ አገሮች ምክትል አስተዳዳሪና የኤርትራ ጉዳይ ልዩ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር መሃሪ መአሾ (ሻለቃ) ገለጹ።

መሃሪ መአሾ (ሻለቃ) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አፋሮች ለኢትዮጵያ አንድነት የታገሉና ለምስራቅ አፍሪካ ሕዝቦች ትስስር መጎልበት ከፍተኛ ሚና የሚወጡ ሕዝቦች በመሆናቸው አስፈላጊው ዕውቅናና ክብር ይገባቸዋል።

አፋር ካለው መልከአምድራዊ አቀማመጥ አኳያ በታሪኩ ከብዙ የውጭ ወራሪዎች ጥቃት ደርሶበታል። ይሁንና ጥቃቶቹን በመመከት የኢትዮጵያን አንድነት እንዲሁም ሉዓላዊነት በማስጠበቅ ረገድ ሰፊ ተጋድሎ ያደረገ ሕዝብ ነው ብለዋል።

ዋነኛው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መስመር የሆነውን የጂቡቲ ኮሪደርን የያዘው አፋር አበርክቶዎቹ ይበልጥ ከፍ እንዲሉ ከምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ሕዝቦች ጋር ያለውን ቁርኝት የሚያሳድጉ አገር አቀፍ ስራዎች መከናወን እንዳለባቸው ሻለቃ መሃሪ ገልጸዋል።

እንደ ሻለቃ መሃሪ ገለጻ፤ አፋር ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የምስራቅ አፍሪካን ቀጣና በኢኮኖሚ ተጠቃሚነትና በባህል ስርዓቶች በማስተሳሰር ረገድ የማይተካ ሚና እየተጫወተ የሚገኝ ህዝብ ነው።

አፋሮች ከኢትዮጵያም አልፎ ከጎረቤት ሃገራት ጋር በባህልና በቋንቋ ሰፊ ማህበራዊ ቁርኝት ፈጥረው መኖርን ባህል አድርገውታል። በኢትዮጵያ ያሉ አፋሮች ከኤርትራና ከጂቡቲ እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች ከሚገኙ ዜጎች ጋር ሰላማዊ ግንኙነታቸውን አጠናክረው በመቀጠል ረገድ ለሌላውም ዓርአያ የሚሆን ስራ እያከናወኑ ነው ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ በአገር ሽማግሌዎች፣ በሐይማኖት መሪዎችና አጠቃላይ ሕበረተሰቡን ባሳተፉ ባህላዊ ስርዓቶችን በመጠቀም የምስራቅ አፍሪካ አገራት የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እንዲጠናከር እንዲሁም ቀጣናው የተረጋጋና ሰላማዊ እንዲሆን ሰፊ ስራ አከናውኗል ሲሉ ተናግረዋል።

የሰው ልጅ ዝርያ መገኛና የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም መዳረሻ የሆነው አፋር የታማኝነት፣ አገርን በጽኑ የመውደድና እንግዳን የማክበር ትውፊቶቹን በማሳደግ ለአገራዊና ቀጣናዊ ጉዳዮች የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ መደገፍ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

አፋሮች እንኳን እኛ ግመሎቻችንም የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ያውቁታል የሚል አባባል አላቸው። በእያንዳንዱ ስራቸው መሃል ለአገር አንድነት የመቆርቆር ስሜትን እያዳበሩ ያድጋሉ። ይህን ልምዳቸው ወደቀጣዩ ትውልድ ለማሻገር በትምህርት ቤቶች አካባቢ ይበልጥ መስራት ይገባል ሲሉ ሻለቃ መሃሪ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

በተለይ ባህላዊ እሴቶቻቸውንና የአገር ፍቅር ስሜቶቻቸውን የሚያሳዩባቸውን መንገዶች፣ ለዕውነትና ለታማኝነት ያላቸውን ጽኑ ፍላጎት እንዲሁም እንግዳ ተቀባይነታቸውን በተመለከተ ትውልዱ ይበልጥ እንዲገነዘበው ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ሻለቃ መሃሪ እንዳስታወቁት፤ ትውልዱ የአፋሮችን መስተጋብራዊ ትውፊትና ባህሎችን ጠንቅቆ እንዲያውቅ በመስራት ከኢትዮጵያ አንድነት ባለፈ ለምስራቅ አፍሪካ ቀጣና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር መጠናከር የሚጠቅሙ እሴቶችን በዘላቂነት ማዳበር ይገባል።

# አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጠቅላይ ሚኒስትሩና ባለቤታቸው ከአረጋውያን መጦሪያዬ ጠርተው በዓሉን አብረን እናሳልፍ ይሉኛል ብዬ አንድም ቀን አስቤ አላውቅም ያሉት ወይዘሮ እታገኘ፤ ለቀሪው ዘመኔም ደስተኛ የሚያደርግ ፍቅርን አግኝቻለሁ ሲሉ ተናግረዋል።

ጤናዬም ሆነ ብርታቴ ጥሩ ሁኔታ ላይ በነበረበት ወቅት የተለያዩ ስራዎች ላይ በመሳተፍ አገሬን አገልግያለሁ፤ አሁን ላይ ግን አቅመ ደካማ በመሆኔ ስራም መስራት አልችልም ፤ ረጂና ጧሪም ቤተሰብ በአጠገቤ ስለሌለኝ በችግር ኖሬያለሁ ያሉት ደግሞ ሌላኛዋ የማዕዱ ተካፋይ እማሆይ በላይነሽ ደመቀ ናቸው።

አሁን ላይ አብዛኛውን ጊዜዬን በጾምና በጸሎት ነው የማሳልፈው። ችግረኛ በመሆኔም ድጋፍ የሚያደርጉልኝ ግለሰቦችን አላጣም። ይሁንና የገና በዓልን ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጋር እንዳከብር በመጋበዜ ትልቅ ደስታ ውስጤን ሞልቶታል። ከማዕድ ማጋራቱ ባለፈ በቤተመንግስት ተጠርቶ በክብር መጋበዙ ውስጥን የሚያድስ ስሜት አለው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለድሆች የሚያስቡ መሪዎች ያስፈልጓታል። ቀድሞ በአፄ ሃይለስላሴ ዘመን ልክ ንጉሱ ድሆችን ጠርተው እንደሚያበሉት ሁሉ አሁን ደግሞ በቤተመንግስቱ ደጅ ግብር መደረጉን አስረድተዋል።

እኔም በመጦሪያዬ ዘመን የበዓል ቀኑን በተከበረ ሁኔታ በጠቅላይ ሚኒስትሩና በቀዳማዊት እመቤት እጅ መስተናገዴና በዓሉን ማክበር በመቻሌ የሚያስብልኝ ሰው የሚያስብልኝ መሪ አለኝ ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል ሲሉ ተናግረዋል።

ሁሉም በየአካባቢው ልክ እንደዚሁ እየተረዳዳና እርስ በእርስ እየተከባበረ ጊዜውን ቢያሳልፍ ችግር አይኖርም። ወገን ዘመድ የለኝም ብለው የሚጨነቁ አረጋውያንና አቅመ ደካሞችም ተገቢውን ፍቅርና እንክብካቤ ካገኙ ቀሪውን ዘመናቸውን ደስተኛ ሁነው እንዲያሳልፉ መረዳት ይቻላል ብለዋል።

ወጣት ደምስ አበራም በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይና በቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው የበዓል ማዕድ ማጋራት ከተደረገላቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች መካከል አንዱ ነው።

ቂርቆስ አካባቢ ከጓደኞቹ ጋር በደሳሳ ቤት ውስጥ የሚኖረው ወጣቱ፤ እግሬ ላይ በደረሰብኝ የአካል ጉዳት የተነሳ እንደልቤ መንቀሳቀስ አልችልም ይላል። በዚህ የተነሳ እንደፈለግኩት ተሯሩጬ የግል ስራዬን መስራት ስለማልችል የኑሮዬ ሁኔታ ከእጅ ወደአፍ ነው ሲል ተናግሯል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩና ባለቤታቸው ግን ለበዓሉ ጥሪ አድርገውልኝ ማዕድ ተጋርቻለሁ። ለዚህ ያበቃኝንም አምላክ አመሰግነዋለሁ። ማዕድ ማጋራቱ እንደቀላል ነገር ሊታይ ይችላል። የእኔን ስብዕና ትልቅ አቅም የሚፈጥርልኝ እንደሆነ አስባለሁ ብሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው የእየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ ለአረጋውያን፤ አካል ጉዳተኞችና የጎዳና ተዳዳሪዎች ትናንትና ማዕድ አጋርተዋል።

በማዕድ ማጋራቱ የተሳተፉ ወገኖች ብዛታቸው 150 ሲሆኑ፤ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለተጋባዦቹ መልካም የልደት በዓልና ማዕድ እንዲሆንላቸው መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል።

# በጥር ወር ስሚጀመረው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አጠቃላይ ዝግጅት ተደርጓል። በጥር ወር ሁሉም ክልሎች ወደተፋሰስ ልማት ሥራ ይገባሉ።

ግብርና ሚኒስቴርም የተፋሰስ ልማት ሥራው በጥራት መሰራቱንና አስፈላጊ ድጋፎችም ዝግጁ መሆኑን ገልጸው፤ ሚኒስትሩ ባሉሙያዎችን በማሰማራት ዋና ዋና በሆኑ በቦታው ተገኝቶ ክትትል እንደሚያደረግ አመልክተዋል።

በጉዳት ከልማት ውጭ የሆነን መሬት በአፈር ጥበቃ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የተመልሶ እንዲያገግም የማድረግ ሥራም ባለፉት ሶስት ዓመታት መሥራቱንም ጠቁመዋል።ይህም እንደሀገር ለተያዘው ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ጥረትም ትልቅ አስተዋጸኦ መኖሩንም ጠቅሰዋል።

ከሁለት ዓመት በፊት መተግበር በጀመረውና ለአምስት ዓመት የተቀረፀው የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት፤ማህበረሰቡ በህብረት ሥራ ማህበር ተደራጅቶ እንዲሳተፍ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፣አርሶ አደሮች በፕሮጀክቱ ድጋፍ ተደርጎላቸው በራሳቸው አቅደው እንዲንቀሳቀሱ መደረጉንም አመልክተዋል። ቀደም ሲል ተስተውሎ የነበረውን የባለቤትነት ማጣት ክፍተት ለመቅረፍ እንደ አንድ ስልት ተይዞ እየተሰራ መሆኑንም አስረድተዋል። በተፋሰስ ልማት በአማካይ አንድ ተፋሰስ አምስት መቶ ሄክታር እንደሚሆን የጠቆሙት አቶ ዮሴፍ፤ይሄ በአምስት ሺህ የተፋሰስ ማህበረሰብ ሲሰላ ሽፋኑ ከፍተኛ እንደሆነም አመልክተዋል።በሌሎች ፕሮጀክቶች የሚከናወነው ሲጨመር ደግሞ የተፋሰስ ልማቱ ሽፋን ሰፊ ይሆናል ብለዋል።

የተፋሰስ ልማት ሥራው በበጋ እንደእርከን ስራ ያሉ ስራዎችን ፤በክረምት ደግሞ የችግኝ ተከላ ተግባራትን የሚያካትት ያልተቋረጠ እንቅስቃሴ መሆኑን አስረድተዋል።

ሚኒስቴሩ የክትትል ሥራውን ለማጠናከር የመረጃ ቋት ወይንም መሰብሰቢያ ሥርአት (ዳታቤዝ) መዘርጋቱንና በዚህ ዘዴም መረጃ ከሁሉም አካባቢዎች ወደ ማእከል እንደሚገባ የገለጹት አቶ ዮሴፍ፤በሀገሪቱ ላይ የሚከናወነውን የተፋሰስ ልማት በመለያ (በኮድ) መዝግቦ ለመያዝም ሥራ መጀመሩን አመልክተዋል።

እንደ አቶ ዮሴፍ ገለጻ፤የተፋሰስ ልማት ሥራ ላይ አንዳንድ ክፍተቶች ቢስተዋሉም ማህበረሰቡ ልማቱን እንደባህል ይዞ ማስቀጠሉ በመልካም ጎን ይጠቀሳል። አረንጓዴ አሻራ መርሃግብርም ለልማቱ አስተዋጽኦ አበርክቷል። መንግሥትም በልዩ ትኩረት እየሰራ መሆኑም ፕሮጀክቶች ድጋፍ እንዲያገኙ አስችሏል። የተፋሰስ ልማት ከ1970ዎቹ ጀምሮ በመንግሥት ፕሮጀክት፣መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በማህበረሰብ ተሳትፎ፣በስፋት ሲከናወን መቆየቱ ይታወቃል።

# የሰላም ስምምነቱን ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሰዎች መቅረብ አለባቸው ነው ያሉት።

ሚዲያው ይህንን ጉዳይ ሰከን ባለ መንገድ ይዞ መዘገብ፣ የአንዱ ልማት የሌላው ጥፋት አድርጎ ከማሰብ አካሄድ መውጣት አለብን ያሉት ዶክተር አብዲሳ፤ እንደአገር መቀጠል በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። በጦርነት አዙሪት እየገነቡ እና እያፈረሱ ከመሄድ መቆጠብ ይገባል ሲሉም መክረዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ችግር ውስጥ እየተገባ ያለው የአንዱ ተስፋ ለሌላው ስጋት፣ የሌላው ስጋት ደግሞ ለሌላው ተስፋ እየሆነ ነው።በመገናኛ ብዙሃን እንደ ምንጭነት ሀሳብ የሚሰጡ ሰዎች አሸናፊና ተሸናፊን መፍጠር የለባቸውም።

ሰላሙ ዘላቂ እንዲሆን አመራሩ፣ ሚዲያውም በኃላፊነት፣ እንደአገር በሚያስቀጥል አስተሳሰብ ላይ ማተኮር አለባቸው። ዘገባዎች የህዝብን አንድነትና አብሮ መኖርን የሚያጠናክሩ መሆን ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በሚዲያ መካከል መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር አብዲሳ፣ ሚዲያው መግባባት ላይ የሚደረስበት አሰራር መከተል፣ የብሄር እና የፖለቲካ ውግንናን በመተው ገንቢ አካሄድን መከተል እንዳለበትም አመልክተዋል።

ይዘቶች በጋራ ተቀርጸው ህብረተሰብን ማሳመን የሚቻልበት፣ አብዛኛው ማህበረሰብ የሚሳተፍበት፣ አንዱ አሸናፊ ሌላው ተሸናፊ የመሆን ስሜትን በማስወገድ የጋራ መግባባት ላይ የሚደረስበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባም አሳስበዋል።

የጋራ መግባባት ላይ እንዲደረስ የውይይት ነጥቦችን በአግባቡ በመቅረጽ በጋራ አሸንፎ መውጣት የሚቻልበትን ሁኔታ ተገናኝቶ መነጋገር ያስፈልጋል ብለዋል።

በጦርነቱ የደረሰውን ጉዳት መልሶ ለመገንባት እና ወደነበረበት ለመመለስ 40 እና 50 ዓመታት ሊወስድ ይችላል። ይህ ደግሞ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳይከተን ኃላፊነት በሚሰማው እና ከወገናዊነት በጸዳ መልኩ ሕዝብን እንደሕዝብ እና አገርን እንደአገር አስቦ መቀጠል የሚቻልበት ውይይትና ተረክ እንዲፈጠር የጋራ መግባባት ላይ መደረስ አለበት ብለዋል።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ራሱን አስከብሮ አገሩን ያነገሰው ሰዓሊ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ኢትዮጵያ በአለም ዋንጫ ለመሳተፍ ባትታደልም በየጊዜው ኢትዮጵያን አጉልተው የሚያሳዩ ኢትዮጵያውያን ግን አልጠፉም። ከእነዚህ ኢትዮጵያውያን መካከል ደግሞ ለዛሬ «የሕይወት ገጽታ» አምዳችን እንግዳ ያደረግነው ኑሮውን በኳታር ያደረገው ኢትዮጵያዊው ሰአሊ ተሰማ ተምትሜ አስራት ነው።

ተሰማ የአለም ዋንጫው ሲጀመር አንስቶ በጥበብ ሥራው የበርካቶችን ትኩረት አግኝቷል፤ በሥራዎቹም ኢትዮጵያን አስተዋውቋል። ኳታርን ያደመቀበትና ኢትዮጵያ በአለም ዋንጫው ገዝፋ እንድትታይ ያደረገበት ሥራውን አሀዱ ያለው ለኢትዮጵያ የእግር ኳስ አባት፣ የቀድሞው የቅዱስ ጊዮርጊስ ባለውለታ፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌድሬሽን የበላይ ጠባቂ እንዲሁም የካፍ ፕሬዝዳንት በመሆን ላገለገሉት ታሪካዊው የስፖርት ሰው አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ስዕል ነው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አፍሪካዊቷ ሀገር ሞሮኮ በኳታር አደባባይ ላይ እንድትደምቅ ካደረጓት መካከል እርሳቸው በዋናነት ይጠቀሳሉና ነው። ለዚህ ውለታቸውም በስማቸው የስፖርት ማዕከል እስከመሰየም ተደርሷል። እናም ሁሉም አፍሪካዊ ተደስቶ ሞሮኮን በደገፈበትና በግማሽ ፍጻሜ ከአራቱ ውስጥ ሆና በገባችበት ወቅት ሰዓሊውም እርሳቸውን ይዞ ብቅ አለ።

«እኔ የእርሳቸው ልጅ ነኝ፤ ኢትዮጵያ እንዲህ አይነት ልጆችን ታፈራለች» እያለም ሰበከ። አለምም ሰማው፤ ተደነቀበት። መነጋገሪያም ሆኖ ሰነበተ። ሞሮኮ የአለም ዋንጫ ግማሽ ፍጻሜ ደርሳ ታሪክ ስትሰራ ትልቁን ሚና የተጫወተውን ኮከቧን ሀኪም ዚያችን ከሳለበት ምስል ስር የይድነቃቸውን ምስል አሳርፎበትም ነበር ብቅ ያለው። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያን አስከብሯታል። ለዚህ ሥራው ደግሞ በታዋቂው የኳታር ኢንተርናሽናል አርት ፌስቲቫል (QIAF) ላይ የአፍሪካ ብራንድ አምባሳደር ለመሆን በቅቷል። ማፐስ ኢንተርናሽናል የሚባል ትልቅ የአርት ተቋምም እንዲሁ በኳታር የአፍሪካ ብራንድ አምባሳደር አድርጎታል። ለ2022 የዓለም ዋንጫ ላይ በበጎ ፈቃደኝነት እንዲያገለግሉ ከተመረጡ ኢትዮጵያውያንም አንዱ ሆኗል።

እ.ኤ.አ በ2022 ላይ በተካሄዱት የኳታር ኢንተርናሽናል የአርት ፌስቲቫሎች ዓለም ዋንጫውንና አዘጋጇን ኳታር በሚያስተሳስሩ ጭብጦች የሰራቸው ስዕሎች በኳታር ንጉሳውያን ቤተሰቦች፤ መንግስታቸው፤ የስነጥበብ ተቋማት መሪዎችና የኢትዮጵያ ማህበረሰብም ተደንቀውበታል። ምስጋናም ተችሮታል። በዚህ ሥራው ኢትዮጵያን በልጆቿ እንድትኮራም አድርጓታል። ምክንያቱም በያሉበት ቦታ ዲፕሎማት የሚሆኑና ስለአገራቸው የሚሰብኩ ልጆች እንዳሉ አንዱ ማሳያ ሆኗል። ለመሆኑ ተሰማ ማን ነው፤ አስተዳደጉና ሌሎች የሰራቸውስ ሥራዎች ምን ይመስላሉ ካልን መልሱን እንካችሁ።

## ትንሹ ተሰማ

ተወልዶ ያደገው በአዲስ አበባ ከተማ ነው። እንደማንኛውም ልጅ ቤተሰቡንና ጎረቤቶቹን በመታዘዝ የልጅነት ጊዜውን አሳልፏል። በተለይም ትልልቅ ሰዎችን ሲያገኝ አይቶ ማለፍ አይሆንለትም። የተሸከሙትን ተቀብሎ ፣ የደከሙትን ደግፎ ቤታቸው ያደርሳል። ከአዘዙትም በደስታ ይላካል። ይህ ባህሪው ደግሞ የዳበረው ከእናት አባቱ እንዲሁም እንደናትና አባት ሆነው ከአሳደጉት ጎረቤቶቻቸው የተማረው ነው። አሁንም ድረስ ከእነርሱ የወረሰው ነገር እንዳለ ያስባል።

በተጨማሪ መልካም ስብዕናውን ያዳበረበት ሌላው ቦታ የቄስ ትምህርት ቤት ሲሆን፤ ከትምህርቱ ባሻገር ብዙ መልካም ነገሮችን ተምሮበታል። ኢትዮጵያዊነትን በሚገባ ያየበትና የኖረበትም ሆኖለታል። ዛሬ እንዳይቸገር ለሰዎች መልካም እንዲሆን ያስቻለውም ይህ ነገሩ እንደሆነ ያምናል።

ተሰማ በሥራዎቹ ሁሉ ከመልካምነት ውጪ ሌላ እንዳያስብ ያደረገው መልካሙን ሁሉ እየተማረ በማደጉ ነው። በተለይም በሥዕል ስራው ውስጥ የሚንጸባረቀው ነገር በሙሉ ሰላም ብቻ እንዲሆን ያደረገው በዚህ አስተሳሰብ መቀረጹ እንደሆነ ያምናል። የልጅነት ፍላጎቱም በዚህ ላይ የተንጠላጠለው ለዚህ ነው። እርሱ ስዕልን መሳል ሲጀምር መጀመሪያ የሳለው መልካም አብሳሪዋንና ሰላም ምሳሌዋን እርግብን ነው። ከዚያ በጎነት የበዛበትን የገጠሪቱን ኢትዮጵያ መሰባሰብ ወደማሳየቱ ገባ።

ትንሹ ተሰማ የህጻናት መዋያ በሚቆይበት ጊዜም ሥዕል መለያው ነበር። በጣም የሚያስገርመው መምህሩ ጻፉ ያሏቸውን ቃላትና ፊደላት ሳይቀር ከማንበብ እና ከማጥናት ባሻገር በስዕል መልክ ፊደላቱን ያስቀምጣቸው ነበር። ይህ ሁኔታው ደግሞ የወደፊቱ ባለተሰጥኦ እንደሆነ ፍንጭ ያሳየበት ነው። ምክንያቱም በጣም በሚወደው ሥዕሉ አማካኝነት ትምህርቱን መከታተል መቻሉ ነው።

ትምህርት

ተሰማ ትምህርቱን አሀዱ ያለው በቄስ ትምህርትቤት ሲሆን፤ ቀለም ከለየና በቄስ ትምህርት የሚፈልገውን እውቀት ከጨበጠ በኋላ መዋለ ሕጻናት ገባ። ከዚያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ለመከታተል ኮተቤ አካባቢ በሚገኘውና ብዙዎችን በአፈራው ደጃዝማች ወንዲራድ ትምህርት ቤት ገባ። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንም በዚሁ ትምህርትቤት ነው ያጠናቀቀው። በዚህ ቆይታው ደግሞ የደረጃ ተማሪ ብቻ ሳይሆን በስዕል ጥበቡ ትምህርት ቤቱን የሚያገለግል ልጅ ነበር። ለትምህርት አጋዥ የሆኑ ስዕሎችን በመሳል አበርክቶ አድርጓል።

ይህ ብቃቱ ደግሞ ከልጅነት ሕልሙ እንዳይወጣ አድርጎታል። እናም የ12ኛ ክፍል ውጤቱ ጥሩ ቢሆንም ሌሎች የትምህርት መስኮችን ለመምረጥ አልፈለገም። በስዕሉ መስክ ለመማር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ጥበባት እና ዲዛይን ትምህርት ቤት በአሁኑ አለ ፈለገ ሰላም የስነጥበብ ትምህር ቤት ተመዘገበ። በመጨረሻም በግራፊክስ ጥናት የትምህርት መስክም ለመመረቅ ቻለ። ለስዕልና ግራፊክስ ሥራውም አጋዥ የሆኑ የተለያዩ ስልጠናዎችን ወስዷል። አሁንም በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረቱ። ምክንያቱም በእርሱ እምነት ትምህርት ሕይወትም፣ ለውጥም ነው።




## ከአዲስ አበባ እስከ ኳታር

ሥራ ከተባለ ጅማሮው የሚሆነው በትምህርት ላይ እያለ የሚያዘጋጃቸው የስዕል ኢግዚቢሽኖች ናቸው።በብሄራዊ ሙዚየም ስዕሎቹን የማሳየት እድል ገጥሞትም እንዲሁ የተሻሉ እድሎችን ያገኘበት ነው። በህፃናትና ወጣቶች ማዕከል እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጀምሮ በፈረንሣይ እና ጣልያን የባህል ማዕከላት በተጨማሪም አዘጋጅቶ በአፍሪካ ህብረት (OAU) እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት UNHCR, UNDP,UNICEF, UNESCO, UNV ጋር በመተባበር በርካታ ስራዎችን ሰርቷል ።

ከዚያ በቅጥር ደረጃ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥራውን ጀመረ። ይህም ቢሆን በምርጫ የተከናወነ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከ60 አመታት በፊት ለአውሮፕላኑ ዲዛይነር የሚቀጥረው ከአዲስ አበባ የስነ-ጥበባት እና ዲዛይን ትምህርት ቤት የተማረና የተሻለ ውጤት ያለውን ሰዐሊ ነው። በወቅቱም በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዕጩ ሰዓሊያን መካከል ከተመረጡት ሦስት ሰዎች መካከል አንዱ ሆኖ ሊቀጠር ችሏል። ለአምስት ዓመትም አገልግሏል። በዚያ ጊዜም ቢሆን ያለውን እድል በመጠቀም የሀገር ገፅታ ግንባታ ላይ ይሳተፍ ነበር።

ተሰማ ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ሰፈር ውስጥ መሸለም፣ መመረቅና መታዘዝ የለመደ በመሆኑ ያ ልምዱ እንዲቆም አይፈልገም። ሰዎች ባያደርጉለት እንኳን እርሱ አድርጎ ይህንን መልካም ነገር ማጎልበት ይፈልጋል። በዚህም በአየር መንገድ እየሰራ ከበርካታ ሀገራት ኤምባሲዎች ጋር ይገናኛል። የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ በሚያደርጓቸው መልካም ነገሮች ስዕልን በመጠቀም ለመልካም ሥራዎቻቸው ያመሰግናቸዋል። በዚህም ሁልጊዜ ከፍተኛ አድናቆት ይቸረዋል።

ለአምስት ዓመት በኢትየጳጵያ አየር መንገድ ኤርክራፍት ፔንቲንግ ዲፓርትመንት (የአውሮፕላኑ አርማ ላይ፤ ከቦዲውና ከሴፍቲ ጋር የተያያዙ ስራዎች) ከሰራ በኋላ የተሻለ እውቀት እና ልምድ ለማካበት ወደ ኳታር በማቅናት ኑሮውን በዚያው አደረገ። ሀሳቡ ተሳካለትና በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነት አገኘ። በእርግጥ ይህ ነገር የሆነለት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባለው ታላቅ ስም እንዲሁም ባካበተው ልምድ ነው። እናም ልክ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ይሰራ እንደነበረው ሁሉ ኳታር አየር መንገድም ኤርክራፍት ፔንቲንግ ዲፓርትመንት መስራት ጀመረ።

አሁን በ ኳታር አየር መንገድ ስራውን በመስራት ላይ ይገኛል።ተሰማ በአየር መንገድ ሥራው ብቻ የታጠረ አይደለም። ከዚያ ጎን ለጎን ከሙሉ ሰዐሊ በማይተናነስ መልኩ በኳታር ውስጥ ባሉ የስዕል ማዕከላት ውስጥ ይሳተፋል። ኢግዚቢሽን ያዘጋጃል። ምንም እንኳን ኑሮው ኳታር ቢሆንም የተለያዩ የአውሮፓ ሀገራትን በሥዕል ሥራው ጎብኝቷል። ለምሳሌ:- ጣልያን፣ እንግሊዝ ፣ ስዊድን፣ፈረንሳይ፣ ሆላንድ፣ አየርላንድ፣ጅቡቲ፣ በመሄድ የስዕል ኢግዚቢሽን አዘጋጅቶ አገሩን አስተዋውቋል።

በኳታር ውስጥ ቀደም ሲል የፊፋ የአረብ ሀገራት ዋንጫ በበጎ ፍቃደኝነት አገልግሏል። በዚያ ባሳየው የበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎቱ ደግሞ ለኳታር የ2022 የአለም ዋንጫ በጎ ፍቃደኛ ሆኖ እንዲመረጥ አድርጎታል። ከሀገሪቷ ንጉስ ሼሕ ታሚም ቢን ሐማድ አልታኒ ኸሊፋ የምስጋና ደብዳቤ ተበርክቶለታል። ከዚህም በተጨማሪ በስነጥበቡ ዘርፍ በኳታር ለተከታታይ አራት ዓመታት ማፐስ ኢንተርናሽናል በሚባል ትልቅ የአርት ተቋም በስነጥበቡ ዘርፍ ባበረከተው አስተዋጽኦ በኳታር የአፍሪካ ብራንድ አምባሳደር በመባል ትልቅ ክብርን አግኝቷል። ይህ ደግሞ በግሉ አፍሪካን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርግ አግዞታል። በተለይም አገሩ ኢትዮጵያ ልዩ ትኩርትን እንድታገኝ ከማድረግ አኳያ የድርሻውን እንዲወጣ እድሉን ሰጥቶታል።

## የሥዕል ዲፕሎማሲነት

ዲፕሎማሲ ማለት ውጤታማ በሆነ መንገድ ከሌሎች ሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታ ነው። በተለያየ ተወካዮች መካከል የፖለቲካ ግፊት ሳይኖር የሚደረግ የድርድር ጥበብ ነው ይባላል። በአለም አቀፍ ዓይን ሲታይ ደግሞ ዲፕሎማሲ የተለመዱ ጉዳዮች የጦርነትና ሰላም፤ የንግድ ግንኙነቶች፤ የኢኮኖሚ፣ ባህልና የሰብአዊ መብት ጥበቃ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ተደርጎ ይወሰዳል። እናም ሰዐሊ ተሰማ እነዚህን ነገሮች አስተባብሮ ከመስራት አኳያ ያስመሰግነዋል። ምክንያቱም በሙያው አገሩን አሳውቋል። መልካሞችን የምታፈራውን ኢትዮጵያን በአለም መድረክ ላይ ከፍ አድርጓታል።

ኢትዮጵያ በራስ መተማመን ስሜት የምትጓዝና ነገሮችን በምክንያታዊነት የምታሳልፍ መሆኗን ለማሳየትም ሞክሯል። እንዴት ከተባለ መጀመሪያ የምናነሳለት እድሎችን በመጠቀም ኢትዮጵያ ማን ናት የሚለውን የገለተጠበት መንገድ ነው። ይህም በኳታር በተካሄደው የአለም ዋንጫ ላይ አጀብ ያስባለው ሥራው ነው።

ተሰማ « አንድ ሰዓሊ በአካባቢው የሚያሸተውን፤ የሚሰማውን እና የሚያየውን ነገር ፈጥኖ ይመለከታል። የሚስለውም ከዚህ በመነሳት ነው። ስለዚህም ኳታር እ.ኤ.አ በ2010 የአለም ዋንጫን ለማዘጋጀት ካሸነፈችበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ፈተናዎች ገጥመውታል። በጎረቤት ሃገራት ማለት ነው። እንደ ሰዐሊ ያንን ችግር በተለያየ የአሳሳል መንገድ በመጠቀም አጉልቶ በማውጣት ለኳታር ያለኝን ምልከታ ሳንጸባርቅ ቆይቻለሁ። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ለኳታር ያላቸው ምልከታ ምን እንደሚመስል ያሳየ ነበር። የሚያስገርመው እነዚያ የሰራኋቸው ሥራዎች ትንቢታዊ ነገር ሆነው ኳታር በብቃት አስደናቂ በሆነ መልኩ የዓለም ዋንጫውን ማዘጋጀት ቻለች። በዚህ የኳታር መንግስት እጅግ ተደስቶ ነበር። ይህ ግን ጎልቶ የወጣው ከአለም ዋንጫ ጋር ተያይዞ ለየት የሚያደርገውን ሥራ ይዤ በመውጣቴ ነው» ይላል።

የኳታር አለም ሲጀመር ስታዲየሞቹ አካባቢ በመሄድ የየሀገራቱን ደጋፊና ታዋቂ ተጫዋቾችን በቀጥታ በሃያ እና በሰላሳ ደቂቃ ውስጥ በመሳል ለደጋፊዎች ትልቅ ድጋፍ በማድረግ አስገራሚ ትዕይንት ፈጥሯል። ሞሮኮ ከአስመዘገበችው ከፍተኛ ውጤት ጋር ተያይዞ የሳለው ስዕልም እውቅናን አስችሮታል።

« እጅግ የተከበሩ ይድነቃቸው ተሰማን ታሪክ በዚህ የአለም ዋንጫ ላይ ማስቀመጥ መቻሌ በሀገሬም ሆነ በሞሮኮ ህዝብ እንዲሁም ፕሮግራሙን ለመሳተፍ በመጣው በርካታ ማህበረሰብ ውስጥ ደስታን መጫር ችያለሁ። ለአፍሪካ የእግር ኳስ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ትልቅ አባት በመሆናቸውም ሁሉም ሰው እንዲያከብረኝ ሆኜበታለሁ። በተለይም ሞሮኳዊያን በእጅጉ ተደስተውብኛል። በአፍሪካ ካርታ ውስጥ የሞሮከውን እግር ኳስ ተጨዋችና እርሳቸውን በማድረግ በመሳሌም ልዩ ምስጢራዊ መልዕክት እንዳስተላለፍኩ ይሰማኛል» ብሏል የነበረውን ሁነት ሲያብራራ።

ይህ ሥራው በሚኖርበት ሀገር እና በሚሰራበት መስሪያቤት ከፍተኛ የሆነ አድናቆትና ክበር ያገኘበትም እንደነበር ያወሳል። በርካታ ሽልማቶችም

**ማህበራዊ**

# የሕይወት ገጽታ

ተበርክተውለታል። በተለያዩ ሚዲያዎችም ላይ ከፍተኛ ሽፋን የተሰጠው ሲሆን ኳታር ፔኒንሱላ፣ በአውስትራሊያ፣ የጀርመን ድምፅ ሬዲዮ፣ ዘሃበሻና በኢትዮጵያዊያን ሚዲያዎች የስዕል ሥራውን ከፍተኛ ሽፋን ተሰጥቶታል። በመሆኑም ለእርሱ ልዩ ነው የሚያስብለው አገሩን ማስተዋወቁ እንደሆነ ያስረዳል። አገሩን በማክበሩ ደግሞ እጅግ ደስተኛ ነው። እርሱ እንደሚለው አገርን ከፍ ማድረግ ራስን ማጉላት ነው። በከፍታውም መሸለም ነው።

‹‹ ዲፕሎማት የመግባባት ችሎታ ያለው እና ሁሉን አቀፍ የዳበረ ስብዕና ያለው ሰው ነው። ተፈጥሯዊ ባህሪን ወደ ተግባር መቀየርንም ይጠይቃል። ስለዚህም ዲፕሎማሲያዊ አገልግሎት ሰጥቻለሁ ስል በእነዚህ መለያ ባህሪያቱ አማካኝነት ነው። ምክንያቱም አንድ ዲፕሎማት በቂ ትምህርትና ስለ ሀገሩ ባህል እምቅ ችሎታ ያስፈልገዋል። ያለን የተጠራቀመ አቅም መጠቀምንም ይጠይቃል። ይህ ደግሞ በታሪካዊ ልምድ መጎልበት መቻል አለበት። እናም እኔ ይህንን አድርጌዋለሁ ብዬ አስባለሁ። በማንኛውም አስቸጋሪ እና ያልተጠበቀ ሁኔታ ውስጥ አልፌ የተሻሉና የሚያስደምሙ ትንግርቶችን እየፈጠርኩ ዛሬ ደርሻለሁ። በቀጣይም በአገሬ ጉዳይ ይህንኑ ሳደርግ እኖራለሁ›› ባይ ነው ሰዓሊ ተሰማ።

አገርን በዲፕሎማትነት ለማገልገል ግድ ከአገር መወከልና አምባሳደር መሆን አይጠበቅብንም። ሁሉም አገሩን የሚወድ ሰው በሄደበት ቦታ አምባሳደርም ዲፕሎማትም መሆን ይችላል። ግድ መሆንም አለበት። ነገር ግን መሰረታዊ የሚባሉ ነገሮችን ማወቅ ያስፈልጋል። በተለይም ዲፕሎማት ለመሆን ምን ይጠበቅብኛል የሚለውን መገንዘብ ግድ ነው። ምክንያቱም ሳናውቀው ልናጠፋ እንችላለን የሚለው ባለታሪካችን፤ የውጭ ሀገራትን ባህል እና ወጎች ማወቅ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባ ነገር እንደሆነ ያነሳል። ምክንያቱም ለአገር ለመስራት በጎነቱ፣ፈቃደኝነቱ ቢኖርም እነርሱን የሚገዛ ሥራ፣ እነርሱን ወደሀሳባችን

የሚያመጣ ተግባር ካልከወንን በስተቀር ራሳችንን አደጋ ውስጥ ከተን አገራችንን ልናስወቅስ እንችላለን።


ስለሆነም ምን ይወዳሉ ፣ምን ይጠላሉ፤ ባህላቸው ምን ይመስላል የሚለውን መርምሮ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ከዚያ የማስታወስ ችሎታችንን ተጠቅመን በከፍተኛ የሥራ አቅምና ግንዛቤ አገራችንን ከፍ ወደማድረጉ መጋበት እንችላለን ሲል ይመክራል።

በአሁን ዘመን አገራት እንዳለፈው ዘመን በየአገራቱ በመደቧቸው አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች ላይ ብቻ ተማምነው ሥራቸውን የሚያከናውኑበት ጊዜ አይደለም። ምክንያቱም ከቴክኖሎጂው መስፋፋት ጋር ተያይዞ የመጣው የዲጂታል ዲፕሎማሲ ቀድሞ የሚሰራቸው በርካታ ተግባራት አሉ። እናም ይህንን ተረድቶ መስራት እንደሚያስፈልግ የሚያምነው ተሰማ፤ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለአገሩ በመጨነቅ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ያከናውናል።

አንዱ ከሰላም ስምምነቱ ጋር በተያያዘ በኳታር ከሚገኙት የደቡብ አፍሪካ፣ የኬንያና የናይጄሪያ ኤምባሲ ጋር ግንኙነት በማድረግ ለሰላሙ ላበረከቱት አስተዋፅጾ የማመስገን ሥራ ለመስራት ተንቀሳቅሷል። ይህም በእንዲህ እንዳለ ለናይጄሪያ ሕዝብ እና መንግስት በኤምባሲው አማካኝነት ያለውን አክብሮት በስዕል አማካኝነት ገልጿል። ‹‹ለአገሬና ለሕዝቤ ላደረጉት መልካም ስጦታ አመሰግናለሁ›› ብሏልም።

የሥዕል ሥራው ‹‹አፍሪካዊያን ለአፍሪካዊያን›› የሚለውን ውህድ የሚያሳይ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደምም ይህንን የተለመደ ተግባሩን ያደርግ ነበር። እናም በአሁኑ ስምምነት ደግሞ በርቱ ለማለት ሁሉንም ሊያስደስት ይችላል ያለውን ስዕል ሰርቶ አበርክቷል። ከቀሪዎቹ ሁለት የአፍሪካ አገራት ጋርም ይህንኑ ተግባሩን ለመከወን የቀጠሮ ጊዜን እየጠበቀ እንደሆነ አጫውቶናል። ለናይጀሪያው አምባሳደር ስዕሉን በሚያስረክብበት ጊዜ ብዙዎች እንደተደመሙ ይናገራል።

ከኢትዮጵያውያኑ አንዱ በስነጥበብ ሙያው አስደናቂ የዲፕሎማሲ ሥራ በማከናወንና የኳታር የዓለም ዋንጫ መስተንግዶ በማሟሟቅ የተሰካለት ሰዓሊ ተሰማ፤ በሌሎች መድረኮች ላይም ዲፕሎማት ሆኖ ያውቃል። ለምሳሌ የ‹‹ኖሞር ዘመቻ›› አንዱ ነበር። ብዙዎችን የማነቃቃትና ለኢትዮጵያ ክብር እንዲቆሙ የማድረግ ሥራ ሰርቶበታል። በተመሳሳይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተሸለሙበት የአረንጓዴ



አሻራ ጉዳይ ላይ ሰፊ ሥራ ሰርቷል። በአካባቢ ጥበቃ ላይ፣ በጤና ላይ በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ስዕልን በመጠቀም ትላልቅ መልዕክትቶችን ያስተላልፋል። ብዙዎቹ ደግሞ ተወዳጅነትን ያተረፉለት ናቸው።

## የሕይወት ፍልስፍና

በመሸለም፣ በመመረቅና በመታዘዝ ያምናል። እነዚህ ሦስት ነገሮች ደግሞ ማንነቱን እንደሚቀይሩትና ከፍ እንደሚያደርጉትም ያስባል። በተለይ ሰዎችን በማክበር በመታዘዝ ራስን ለመሆን መጣር የሁልጊዜ መመሪያው ነው። በእነዚህ መርሆቹ ውስጥ ተጉዞ አገሩን ማኩራትም ዋነኛ ዓላማው ነው። ሁልጊዜ አገር ከራስ ትበልጣለች የሚል መፈክር አለው። ምክንያቱ ደግሞ በአገር ውስጥ ራስን ማድመቅ ይቻላል ብሎ ማሰቡ ነው።

## የቤተሰብ ሁኔታ

ተሰማ ባለትዳርና የአራት ልጆች አባት ሲሆን፤ ሁሉንም በአገሩ ባህልና ወግ አሳድጓቸዋል። ልዩ ተሰጥኦዋቸውን እንዲለዩና በዚያም እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል። እርሱም ሆነ ባለቤቱ ተደጋግፈው የሚሰሩ መሆናቸው ደግሞ ልጆቻቸው በደስታ እንዲያድጉ መሰረት ጥሎላቸዋል። በተለይም ባለቤቱ የሁሉ ነገር ምሰሶ እንደሆነች ያስረዳል። ለዛሬ እዚህ መድረሱ የእርሷ ድርሻ ላቅ ያለም መሆኑን ያነሳል። በተጨማሪም ለስኬቱም ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ትልቅ ሚና ተጫውታለች። ከእግር ኳሱ ጋርም በተያያዘ የልጁ ጸጋዘአብ ተሰማ ልዩ ፍላጎት ገፋፍቶት እንደገባበትና ለዚህ እንደበቃም አጫውቶናል።

## ምኞት

ለሃገሬና ለህይወቴ የምመኘው አንደኛ ወደ ሀገሬ በመመለስ ያለኝን እውቀት ለወገኔ ለህዝቤ ማድረስን ነው። አዲሱ ትውልድ በአዲስ አስተሳሰብ እንዲራመድ የአቅሜን ማበርከት እሻለሁ። ያለኝ እውቀት ልምድ የወገኔ እንዲሆን እፈልጋለሁ።

በሁለተኛ ደረጃ ስዕል በመሳል የተለያዩ አስተማሪ የሆኑና ተፅዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ ሥራዎችን ማከናወን ምኞቴ ነው። በተለይም በአካባቢ ጥበቃ፣ በጤናና ማህበረሰባዊ አገልግሎት ላይ ትኩረት ባደርግ ደስ ይለኛል። ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች አገርን ከፍ አድርገው ትውልድን ያንጻሉ። በመስራት የሚደሰት ማህበረሰብንም ይፈጥራሉ።

## ስዕልና እይታው

‹‹ ስፖርትና ኪነጥበብ የተለየ ገጽታ ያላቸው ነገሮች አይደሉም። ሁሉም ሰላምን መስበኪያና የተረጋጋች አገር መፍጠሪያ ናቸው። አገርን በኢኮኖሚ ማበልጸጊያም እንደሆነ እሙን ነው። ምክንያቱም በስፖርት ሰበብ ብዙ ቱሪስት ወደ አገር ውስጥ ይጎርፋል። እናም ከፍተኛ ገንዘብ መሰብሰብ ይቻላል። በዚያው ልክ ባህልን ማስተዋወቂያና ማንነትን መስበኪያ ነው። የእርስ በእርስ ትስስርን ማጎልበቻም ነው።

እናም እድል ማግኛ ስለሆነ ለተጠቀመበት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማንነትን ይገነባል፤ ይገልጣልም። ላልተጠቀመበት ደግሞ በተቃራኒው ይሆናል። እኛ በሰው



አገር ላይ ሆነን ሳይቀር አገራችንን መግለጥ የቻልነው የእድል ትርጉሙ ስለገባን ነው።›› የሚለው ተሰማ፤ በኳታሩ አለም ዋንጫ ከ51 በላይ የስነጥበብ ባለሙያዎች 102 የስዕል ሥራዎችን ባቀረቡበት ኤግዚብሽን ላይ የስዕል ሥራዎቹ በልዩ ጭብጡ አነጋጋሪ ሆነውለታል። ምክንያቱ ደግሞ ስዕልን የሚያይበት እይታ ነው።

እንደሱ እምነት ስዕል የሕይወት መመሪያ ነው። የጤንነት ስሜት መለኪያና ማረጋገጫ ነው። ሰላም መግዢያና ለሌሎችም ማጋቢያ ነው። ስዕል ከሌሎች ጋር መግባቢያና መቀራረቢያ ቋንቋ ነው። ሰው ማግኛ፣ ዘመድ ማፍሪያም ነው። አገሬን ማስታወሻና ማሳወቂያም ነው። ቤተሰቤንና ራሴን ማኖሪያም ጭምር ነው። በአጠቃላይ ስዕል ሕይወት ነው ይላል።

## መልእክት

ኢትዮጵያዊያን ከኢትዮጵያ ሲወጡ የራሳቸውን ማንነት ማስከበር ላይ በእጅጉ መጣር አለባቸው። በተለይም ወደ አረብ አገራት የሚጓዙት። በትክክለኛው መስመር ወጥተው አቅማቸውን ማሳየት ላይ መስራት ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ያን ጊዜ የሚኖራቸው ክብር የማይናድ ይሆናል። ለራሳቸው ሆነው ለአገራቸው የሚያተርፉም ያደርጋቸዋል። ከአገር የሚወጣው ተለውጦ ለመመለስ እንጂ ለመንከራተትና የውሃ አለያም የሞት ሲሳይ ለመሆን አይደለም። እናም መስመሩም መንገዱም ለውጥ በሚያመጡበት ላይ መሆን ይገበዋል የመጀመሪያ መልዕክቱ ነው።

ሌላው ከሰላም ስምምነቱ ጋር ተያይዞ ያነሳው ጉዳይ ሲሆን፤ ኢትዮጵያዊያን ሰላም ወዳድና ባለታሪክ ሕዝቦች ናቸው። ከብዙ አገራት የሚለዩትም በይቅር ባይነታቸው ነው። ስለዚህም አሁን በስምምነቱ የአደረጉትን መልካም ነገር በሁሉም ተግባራቸው ሊያረጋግጡት ይገባል። ለዚህ ደግሞ ሁሉም በሙያው ማገዝ ይኖርበታል። ምክንያቱም በአንድ እጅ ማጨብጨብ አይቻልምና።

# የአገር ውስጥ ቱሪዝም- በገና እና ጥምቀት

**ዳግም ከበደ**

የኢትዮጵያ መንግስት የቱሪዝም ዘርፉን የሀገሪቱ የምጣኔ ሃብት ምሰሶ በሚል ከያዛቸው አምስት ዘርፎች መካከል አንዱ አርጎታል። ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ የተሰጠውን ሚና እንዲጫወትም ስትራቴጂዎችን ነድፎና አደረጃጀት ፈጥሮ እየሰራ ይገኛል።

አገሪቱ በርካታ ባህላዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና የአርኪዎሎጂ መስህብ ሃብቶችን እንዲሁም ሃይማኖትን እንዲሁም ባህልን መሰረት ያደረጉ የማይዳሰሱ እያሌ ሃብቶች ባለቤት እንደመሆኗ መንግስት ለቱሪዝም ዘርፉ ትኩረት መስጠቱ ይህን እምቅ ሀብት ተጠቅሞ ኢኮኖሚውን ወደፊት ለማራመድ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

የቱሪዝም ዘርፉ አመቱን በሙሉ እንቅስቃሴዎች የሚደረጉበት ቢሆንም በመስከረም፣ ታህሳስና ጥር ወራት ግን በርካታ የተለዩ እንቅስቃሴዎች ይደረጋሉ። በመስከረም ወር ሀገሪቱ የዘመን መለወጫዋን የምታከበርበት ከመሆኑ በተጨማሪ በኦሮሚያ የኢሬቻ በአል፣ በደቡብ ክልል ደግሞ በርካታ ብሄሮችና ብሄሰቦች አዲስ አመታቸውን ያከብራሉ። ከእነዚህ ጋር በተያያዘ በርካታ ባህላዊ ስርአቶች የሚካሄዱ መሆናቸውን ተከትሎ በዚህ ወር የቱሪስቶች ፍሰት ከፍተኛ ይሆናል።

በታህሳስና ጥር ወራት ደግሞ ታላላቅ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ክብረ በዓላት ይካሄዳሉ። ይህን ተከትሎም ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ የሚደረገው ጉዞና ከዚያም የሚገኘው ምጣኔሃብታዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። በእነዚህ ወራት በተለይ ከውጪ አገራት ከሚመጡ ቱሪስቶች፣ ትውልደ ኢትዮጵያን በተለየ መንገድ የአገር ውስጥ ጎብኚዎች መጠን በእጅጉ ከፍተኛ ይሆናል።


መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በታህሳስና ጥር ወራት ወደ ሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ያለው የጎብኚዎች ፍሰት ይጨምራል። ምክንያቱ ደግሞ "ገናን በላሊበላ ወቅር አብያተ ክርስቲያናት" እና የጥምቀት "ከተራ" በዓልን ደግሞ በጎንደር ከተማ በልዩ ሁኔታ ለማክበር ከፍተኛ ፍላጎትና ፍሰት ስላለ ነው። ያለፉት ሶስት ዓመታት አሃዛዊ መረጃ ስንመለከት ቁጥሩ እያሻቀበ መምጣቱንም እንረዳለን።


በጎንደር ከተማ ያለውን መረጃ እንደምሳሌ ብንወስድ በእነዚህ የጎብኚዎች ፍሰት በሚበዛባቸው ወራት ጭምር በ2013 በጀት ዓመት የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ቁጥር 57 ሺህ ነበር። በ2014 በጀት ዓመት ይህ አሀዝ ወደ 325 ሺህ አሻቅቧል። በ2014 ዓም ብቻ ከአገር ውስጥ ጎብኚ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል። ይህ መረጃ የሚያሳየን ከውጪ አገራት የሚገቡትን ዲያስፖራዎች፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የውጪ አገራትን ጎብኚዎች ጨምሮ በእነዚህ ወራት ከፍተኛ የአገር ውስጥ ጎብኚዎች ፍሰት ወደ አካባቢው እንዳለ ነው።

የአማራ ክልል በታህሳስና የጥር ወራት በርካታ ጎብኚዎችን ያስተናግዳል። የአማራ ክልል የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ሃላፊ አቶ አባይ መንግስቴ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት መረጃ እንዳስታወቁት፤ ክልሉ ዘንድሮም የገናንና የጥምቀትን በዓላት በታሪካዊዎቹ ጎንደርና ላሊበላ ከተማ ለማክበር የሚመጡ እንግዶችን ለማስተናገድ ሰፊ ዝግጅት አድርጓል። በዚህ ሰሞንም እስከ 750 ሺህ የሚጠጉ ጎብኚዎችን በመቀበልና በማስተናገድ 2 ቢሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት አቅዶ እየሰራ ነው። የዘንድሮውን የገናን በአልም ትናንት በመላው ኢትዮጵያና በተለይ ደግሞ በታሪካዊቷ የላሊበላ ከተማ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምእመናን በታደሙበት በደማቅ ስነስርአት ተከብሯል።

### የልደት በዓልን በላል ይበላ

የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ከሚያነቃቁ ክበረ በዓላት አንዱ የሆነው በተለይ በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በደማቅ ስነስርአት የሚከበረው የእየሱስ ክርስቶስ የልደት/ ገና/ በዓል ትናንት በታሪካዊቷና አስደናቂ ውቅር ዓብያተ ክርስቲያናትን በያዘችው ላል ይበላ ከተማ ተከብሯል። በአሉ በዋናነት ግን ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ወደ ስፍራው በመትመም አስደማሚ ወቅት ማሳለፍ የሚቻልበት በብዙሃኑ ዘንድ በጉጉት የሚጠበቅ ነው። በዚህ ሃይማኖታዊ ይዘት ባለው በዓል





ላይ ከመላው ዓለም የሚመጡ ጎብኚዎች በስፋት የሚገኙ እንደመሆናቸው ዘንድሮም በርካታ የእምነቱ ተከታዮች፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎች በበአሉ ላይ ተገኝተዋል።

ጎብኚዎች በእለተ ገና በላሊበላ ተገኝተው ክብረ በዓሉ ላይ ይታደሙ እንጂ አብዛኞቹ ግን በዚያው ቆይታቸውን ለሁለትና ሶስት ቀናት ያራዝማሉ። ዋንኛ ምክንያታቸው ደግሞ በአካባቢው በከተማዋ የሚገኙትን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሳይንስ የባህልና ትምህርት ድርጅት ዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡትን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ከጫፍ እስከጫፍ መጎብኘት ነው። ከዚያ በተጨማሪ በከተማዋ የሚገኙ (የይምርሃነ ክርስቶስን ታሪካዊ ቤተክርስቲያን ጨምሮ) ልዩ ልዩ ስፍራዎችን ይጎበኛሉ ።በዚህም ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ፍሰት ይደረጋል፤ ከዚህም የቱሪዝም ምርት አገልግሎት አቅራቢዎች፣ አስጎብኚዎች፣ ሆቴሎችና ማህበረሰቡ በእጅጉ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የጸርሐ ቅዱስ ላሊበላ ዓለምአቀፍ ቅርስ ዋና አሥተዳዳሪ አባ ፅጌ ሥላሴ በመገናኛ ብዙሃን የዘንድሮውን ክብረ በዓል የእምነቱ ተከታዮች ወደ ስፍራው እንዲመጡ ጥሪ ባስተላለፉበት መልእክታቸው ላይ አንደተናገሩት፤ በዚህ ዓመትም በዓሉ የቅዱስ ያሬድ ዝማሬና የቤዛ ኩሉ ሥርዓት ዝግጅትን ካሕናት ሲከውኑ መቆየታቸውን ጠቅሰዋል። በተጨማሪም ምእመናን በቤተክርስቲያን ግቢ የሚገኙ የእንግዶች ማረፊያዎችን ማስተካከል እና የውኃና መብራት አገልግሎት እንዲኖር በማድረግ አስፈላጊውን ስራ መስራታቸውን ገልፀዋል። ምእመናን ቤታቸውንና ግቢያቸውን ጨምሮ ለእንግዶች ማረፊያ እንዲሆን ማዘጋጀታቸውንም ጠቁመዋል። የደከሙትን እንግዶች እግር የማጠብ፣ ስንቅ የመስጠት ስነስርዓት እንደሚኖርም ገልፀው ነበር።

"በከተማዋ ለረጅም ጊዜ ተቋርጦ የነበረው የመብራትና የውኃ አገልግሎት ወደ ነበረበት በመመለሱ በዚህ ዙሪያ ችግር የለም" ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ ተዘግተው የቆዩ ሆቴሎች ለእንግዶች አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ መኾናቸውንም ተናግረዋል። የከተማዋን ጸጥታና ደኅንነት ለመጠበቅም ከመንግሥት አካላት ጋር በቅንጅት እየሠሩ እንደኾነ ጠቁመው በዚህ ዙሪያ ምንም አይነት ስጋት አንደሌለ ነው መልእክታቸውን ያስተላለፉት።

አባ ፅጌ ሥላሴ መዝገቡ እንዳሉት፤ የቀደምት አባቶችን ታሪክ ለማስታወስና በረከታቸውን ለማግኘት በርካታ ምእመናን ከተለያዩ አካባቢዎች በእግራቸው ወደ ከተማዋ ገብተዋል። እነሱን ለማስተናገድም አስፈላጊውን ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል። በላሊበላ ዙሪያ በርካታ የሚጎበኙ መንፈሳዊ መዳረሻዎች ስለሚገኙ ምእመናን የቆይታ ጊዜያቸውን አራዝመው ጉብኝት እንዲያደርጉም በወቅቱ ጥሪም አስተላልፈዋል።

የክልሉ መንግስት ስለ በዓሉ ምን ይላል

በዚህ ወቅት ከመቼው ገዜ በተለየ የአገር ወስጥ ቱሪዝም ፍሰቱ ወደ ሰሜኑ ክፍል ይጨምራል። ይህም ለቱሪዝም ምርት አቅራቢዎች፣ ሆቴሎች፣ የሆስፒታሊቲና የማስጎብኘት ተግባር ላይ ለተሰማሩ አካላት ትልቅ ትንሳኤ ነው። በተለይ ከዚህ ቀደም በጦርነትና በወረርሽኝ ምክንያት ተዳክሞ የነበረው እንቅስቃሴ መነቃቃትን እንደሚያሳይ ይጠበቃል። አሀዛዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱትም፤ በተለይ ወደ አማራ ክልል የሚያቀኑ ጎብኚዎች ብዛት ከፍተኛ ነው። በዚህ መሰረት የአማራ ክልል 750 ሺህ ተጓዦች በክልሉ ይገኛሉ ብሎ ዝግጅቱን አጠናቆ እየጠበቀ መሆኑን አስታውቋል።

የአማራ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ በክልሉ ከታኅሣሥ ጀምሮ የሚከናወኑ የተለያዩ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ክብረ በዓላትን አስመልክቶ በሰጠው መግለጫ ላይ የአማራ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ኀላፊ ጣሂር ሙሀመድ እንዳሉት፤ በጦርነቱና በኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ተጎድቶ የነበረውን የቱሪዝም ዘርፍ ለማጠናከር የተሻለ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

በጎንደር ከተማ በተለየ መልኩ የሚከበረውን የጥምቀት በዓል፣ በሰሜን ሸዋ በኢራንቡቲ የሚከበረውን የጥምቀት በዓል፣ በእንጅባራ ከተማ የሚከበረውን የአገው ፈረሰኞች በዓል፣ በደብረ ታቦር ከተማ የሚከበረውን የመርቆርዮስ በዓልና ሌሎች በዓላትም በደመቀ መልኩ እንዲከበሩ ቢሮው ከአካባቢው አስተዳደሮችና ማኅበረሰቡ ጋር እየሠራ መሆኑን ሃላፊው አብራርተዋል።

"በሰከላም ላይ ሚከበረውን የግዮን በዓል በድምቀት ለማክበር ተዘጋጅተናል" ያሉት አቶ ጣሂር ሙሀመድ ለሁሉም በዓላት ለሚታደሙት እንግዶች የቱሪዝም ትውውቅ በማድረግ ዘርፉን የማጠናከር ሥራ እየተሰራ መሆኑን አመላክተዋል። ቢሯቸው ከዓመት ወደ ዓመት የጎብኚዎች ቁጥር እንዲጨምር እየሠራ መሆኑንም ተናግረዋል።

ከሰሞኑ እየወጡ በሚገኙት መረጃዎች መሰረት በልዩ ሁኔታ በሰሜኑ ክፍል የሚከበሩ በዓላትን አስመልክቶ የማረፊያ ስፍራ ስለመጥፋት፣ የዋጋ ጭማሪና ለእለት ፍጆታ የሚሆኑ እቃዎች እየተወደዱ ስለመሆናቸው ይነገራል። ይህንን ፍራቻ ወደ አካባቢው የሚያቀኑ ተጓዦች መጉላላት እንዳይደርስባቸው ስጋታቸውን በማህበራዊ ሚዲያና ሌሎች አማራጮች ሲገልፁ ተሰምቷል። ይህንን ውዥምብር የክሉ አመራሮች ለማጥራት እየሞከሩ ነው።

አቶ ጣሂር ጉዳዩን ለማጥራት በሰጡት መግለጫ ላይ በተለይ በዓላቱ በጎንደርና በላሊበላ ከተሞች ሲከበሩ አላስፈላጊ የዋጋ ንረት እንዳይኖር ከነጋዴው ማኅበረሰብ ጋር ውይይት እንደሚደረግ ተናግረዋል። የዋጋ ንረቱ ቱሪስቶችን ሊጎዳ ስለሚችል አላስፈላጊ የዋጋ ጭማሬ በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ እርምት የመውሰድ ተግባር እንደሚፈጸም አስገንዝበዋል። ነጋዴዎች የበዓላቱን ድባብ ማጠልሸት እንደሌለባቸው አሳስበዋል።

በጥር ወር ብቻ ሳይሆን ዓመቱን ሙሉ የሚመጡ እንግዶች በተለይ የአገልግሎት ዘርፉን ተጠቃሚ ስለሚያደርጉ አስተማማኝ ጸጥታ እንዲኖር፣ የዋጋ ማስተካከያ በማድረግ፣ የአካባቢን ፅዳት በመጠበቅ በኩል ተገቢው የቅድመ ዝግጅት ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን አስረድተዋል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ተግባር የአገር ውስጥ ቱሪዝም እድገት

የቀድሞው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መንግስት ባደረገው ማሻሻያ መሰረት የአደረጃጀት ለውጥ ተደር ጎበታል። በዚህም መሰረት "ቱሪዝም ሚኒስቴር" ብቻውን እንዲደራጅ ተደርጓል። ቱሪዝም ሚኒስቴር በአዲሱ አደረጃጀት ዘርፉን እያንቀሳቀሰ ይገኛል። ይህ ተቋም ከአምስቱ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን ዘርፍ እየመራ ስር ነቀል ለውጥ የማምጣት ሃላፊነት ተጥሎበታል።

ሚኒስቴሩ የመስህብ ሃብቶችን የማስተዋወቅ፣ ገበያ የማፈላለግ፣ የማልማትና የመጠበቅ ተግባር ከማከናወኑም ባሻገር የአገር ውስጥ ቱሪዝምን የማበረታታትና ንቅናቄ የመፍጠር ድርሻውንም መወጣት እንዳለበት ይታመናል። ይህንን ለማስፈፀም ደግሞ ከሰሞኑ "ልወቅሽ ኢትዮጵያ" የሚል ኢትዮጵያውያን ጎብኚዎችን የሚያበረታታ ንቅናቄ ጀምሮ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። አዳዲስ መዳረሻዎችን በማስተዋወቅና ጥቆማ በመስጠት ለጎብኚዎች አማራጮችን ከመፍጠር ባሻገር በታህሳስና ጥር ወራት በተከታታይ በሰሜኑ ክፍል በታላቅ ድምቀት የሚከበሩትን ክብረ በዓላት እንደ ምቹ አጋጣሚ ወስዶ ጎብኚዎች ወደ ስፍራው እንዲያቀኑ እያበረታታ ነው።

የቱሪዝም ሚኒስቴር የገበያ ልማትና ግብይት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ዳዊት የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ኢንዱስትሪው መነቃቃት እያሳየ መሆኑን ይናገራሉ። በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ተከስቶ የነበረው ጦርነት ከኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ጋር ተደምሮ የቱሪዝም ዘርፉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሮ ቆይቷል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተፈጠረው ግጭት ተጽእኖ ካሳደረባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ቱሪዝም ነው ይላሉ።

ሰላም ለቱሪዝም እድገት ቁልፉ መሳሪያ ነው የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ከዚህ አኳያ የሰላም ስምምነቱ ለዘርፉ ወሳኝ ምዕራፍ የከፈተ መሆኑን ይናገራሉ። ይህንን ተከትሎ በታህሳስና በጥር ወቅት የሚከበሩትን የገና እና ጥምቀት በዓል ታሳቢ ባደረገ መልኩ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን የማስተዋወቅ ስራ እየተከናወነ መሆኑንም ተናግረዋል።

በዓሉን ለመታደም ከውጪ አገራት ለሚመጡ እንግዶችና ከአገር ውስጥ ወደ ስፍራው ለሚያቀኑ እንግዶች ላልይበላና አካባቢውን እንዲጎበኙ ፓኬጆች መዘጋጀታቸውን ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል። የሠላም ስምምነቱን ተከትሎ ኢትዮጵያ ያላትን የቱሪዝም መስህብ ለአገር ውስጥና ለውጭ ጎብኝዎች ለማስተዋወቅ እየተሰራ እንደሚገኝም ተናግረው፤ በተለያዩ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በተዘጋጀው መርሃ ግብር ላይ እንዲሳተፉ ሚኒስቴር መሪያቤቱ ጥሪ በማድረግ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ እንደሚገኝ ነው የገለፁት።

### እንደ መውጫ

የቱሪዝም ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የአገር ውስጥ ጎብኚዎችን የማነቃቃት ግብ በስትራቴጂ የተቀመጠ ነው። ለረጅም ዓመት የሚቆይና በስፋት ይሰራበታል። ይህ ስራ በአገራችን እንደ ባህል ተደርጎ እስኪወሰድ ድረስ የሚቀጥል እንደሆነ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተደጋጋሚ ሲገልፅ ይሰማል። ኢንዱስትሪው በተለያዩ ወቅታዊ ምክንያቶች ከገባበት መቀዛቀዝ እንዲላቀቅ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ ስፍራ አዳዲስ መስህቦችን ለመመልከት የሚደረጉ ጉዞዎች እንደ ባህል መውሰድ ይኖርባቸዋል። ለዚህ ደግሞ ገናን፣ ጥምቀትንና መሰል ክብረ በዓላትን እንደ ጥሩ አጋጣሚ መውሰድ ያስፈልጋል።

ከአንድ አካባቢ የሚነሳ ማህበረሰብ በሌላ ጥግ ያለውን የአገሩን ክፍል (በሃይማኖታዊ ጉዞም ሆነ የመስህብ ስፍራዎችን ለመመልከት በሚደረግ መነሻ) በሚጎበኝበት ግዜ ባህሉም ሆነ የአኗኗር ሁኔታው ምን ያህል አንድ አይነትና የተመሳሰለ እንደሆነ የማየት እድልም ይኖረዋል። ይሄ ደግሞ ከኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ባሻገር አንድነትን ለማጠናከር በእጅጉ ጠቃሚ እንደሆነም ይታመናል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊና አፍሪካዊ ጄት አብራሪ

**ዋለልኝ አየለ**

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪካዊ ‹‹የንግድ ጄት›› አብራሪ የሆኑትን ኢትዮጵያዊው ካፒቴን አለማየሁ አበበን እናስታውሳለን። እኚህ ኢትዮጵያዊ ባለ ታሪክ በ93 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም የተለዩት ከአምስት ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 26 ቀን 2010 ዓ.ም ነበር።

ካፒቴን አለማየሁ ገና ከአስር ዓመታቸው ጀምሮ አውሮፕላን በሰማይ ላይ ሲበር ሲያዩ አውሮፕላን አብራሪ የመሆን ሕልም እንደነበራቸው በተለያዩ ጸሐፊያን የተሰነደው ታሪካቸው ያሳያል። ህልማቸውን ለማሳካት ጠንካራ ትጋትና ስነ ምግባር የነበራቸው ካፒቴን አለማየሁ፣ በ1955 ዓ.ም የመጀመሪያውን ‹‹የንግድ (Commercial) ጄት›› በማብረር በዘርፉ ፈር ቀዳጅ ኢትዮጵያዊ እንዲሁም አፍሪካዊ ለመሆን በቅተዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ወደ ጄት ዘመን ሲሸጋገር ከፋና ወጊ አብራሪዎች ተጠቃሹ ካፒቴን አለማየሁ አበበ ነበሩ። የመጀመርያውን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ‹‹ቦይንግ 720B›› አውሮፕላን በካፒቴንነት ያበረሩት ካፒቴን አለማየሁ፣ በዚሁ ተግባራቸው ‹‹የመጀመሪያው›› አፍሪካዊም ናቸው። በኅዳር 1955 ዓ.ም ቦይንግ ጄት ከሲያትል (አሜሪካ) ከቦይንግ ፋብሪካ አውሮፕላኑን እንዲያመጡ የተደረጉት ካፒቴን አለማየሁ አበበ እና ካፒቴን አዳሙ መድኃኔ ነበሩ።

ካፒቴን አለማየሁ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ለመቀላቀል የቻሉት በኢትዮጵያ አየር ኃይል በኩል በማለፍ ነው። በወቅቱ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ውጤት ያጠናቀቁ ተማሪዎች ወደ አቪዬሽን ትምህርት እንዲገቡ ሲደረግ ከዕድሉ ተጠቃሚዎች መካከል አንዱ ካፒቴን አለማየሁ ነበሩ። በ1943 ዓ.ም ምርጥ የሆኑ አብራሪዎች ከአየር ኃይል ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲዛወሩ በተወሰነው መሠረት፣ ካፒቴን አለማየሁ ከተመራጮቹ አንዱ መሆን ችለው የኢትዮጵያ አየር መንገድን ተቀላቀሉ።

በሦስት አስርታት ዓመታት የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአገልግሎት ዘመናቸውም ከመጀመርያ የበረራ መኰንንነት እስከ ካፒቴንነት (ከየመጀመርያው የቦይንግ 720B ጄት ካፒቴንነት) እስከ አየር መንገዱ የበረራ ዘርፍ ምክትልና ዋና ኃላፊነት (ከ1948 እስከ 1960 ዓ.ም) ድረስ ሠርተዋል። ከ1961 እስከ 1972 ዓ.ም. ደግሞ የዓለም አቀፍ በረራዎች ዳይሬክተር፣ የበረራ ኦፕሬሽን ረዳት ጄኔራል ማኔጀር ሆነው አገልግለዋል። በ1968 ዓ.ም. የመጀመርያው አፍሪካዊ የቦይንግ 707 ጄት ካፒቴን ሆነው ሲሾሙ፣ በ1972 ዓ.ም የጄት ካፒቴኖች ፈታኝ በመሆን አገልግለዋል።

ከኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ አገልግሎታቸውን በ1974 ዓ.ም ፈጽመው ከተሰናበቱ በኋላ፣ በኡጋንዳና በየመን አየር መንገዶች ውስጥ በአሠልጣኝነትና በአማካሪነት ለአምስት ዓመታት ያህል ሰርተው የበረራ ምዕራፋቸውን ቋጭተዋል።

ካፒቴን አለማየሁ አበበ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ስራ አስፈፃሚ የነበሩትን ኮሎኔል ስምረት መድኃኔን እንዳስተማሯቸው ታሪካቸው ያስረዳል።

በሦስቱ መንግሥታት ዘመን በከፍተኛ የአገርና የሙያ ፍቅር አገራቸውን ያገለገሉት ካፒቴን አለማየሁ፣ ባለትዳርና የአራት ሴቶችና የአራት ወንዶች ልጆች አባት፣ እንዲሁም የአራት የልጅ ልጆች አያት ነበሩ። ዕውቀታቸውንና ልምዳቸውን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ በማሰብም በ1997 ዓ.ም ‹‹ሕይወቴ በምድርና በአየር›› የሚል መጽሐፍ አሳትመዋል።

በዚሁ እግረ መንገድ ስለኢትዮጵያ አየር መንገድ ታሪክ በጥቂቱ እንቃኝ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የተመሠረተው ከጣልያን ወረራ በኋላ ነበር። የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ተዋናይ የነበረችው ጣልያን በ1933 ዓ.ም ከኢትዮጵያ የአምስት ዓመት ወረራ ተሸንፋ ከወጣች ከአምስት ዓመት በኋላ






በዚሁ በታኅሳስ ወር 1938 ዓ.ም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተቋቋመ።

በአሜሪካ ሠራሽ አውሮፕላኖች የበረራ ሥራ የጀመረው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በጊዜው ከቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ጋር በተደረገ ስምምነት አየር መንገዱን ያቋቋመው ዛሬ ላይ

ገበያ ላይ የሌለው የአሜሪካኑ ትራንስ ወርልድ አቪየሽን TWA (Trans World Aviation) ነበር።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ አስተዳዳሩም በአሜሪካዊያን እጅ ነበር። ዓለም አቀፍ ጉዞውንም አሀዱ ብሎ የጀመረውም ወደ ግብፅ ዋና ከተማ ካይሮ ሳምንታዊ በረራ በማድረግ ነው። ይህም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተመሠረተ በሦስተኛው ወሩ መጋቢት 30 ቀን 1938 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ተነሥቶ ካይሮ ድረስ ያካሄደው ዓለም አቀፍ በረራ ነው፡

አየር መንገዱ ሲመሠረት ከአሜሪካ ወታደራዊ ኃይል የተገዙና በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ያገለገሉ አምስት ዲ.ሲ. 3 (DC 3-C47) አውሮፕላኖች ነበሩት። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራውን ሲጀመር ይገለገልበት የነበረው የአዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ በጦር ኃይሎች በሚባል በሚጠራው ቦታ ሥር የሚገኘውን ማኮብኮቢያ ሜዳ ነበር። ሜዳው ለአውሮፕላን ለመንደርደሪያ በቂ ስላልነበር ቀስ በቀስ ዋና ማረፊያ ጣቢያው ቦሌ ወደ ሚገኘው ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ አዘዋወረ። የጦር ኃይሎችን አንዳንድ ሰዎች አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ በሚል ይጠሩታል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የተመሠረተበትን 75ኛ ዓመት የአልማዝ ኢዮቤልዩ 2013 ዓ.ም አክብሯል። አየር መንገዱ በዓለም ላይ እጅግ ተወዳዳሪ ከሆኑ ግዙፉ ገናና ስምና ዝና ካላቸው ተርታ የሚጠቀስ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአፍሪካ ምርጡና ቀዳሚ አየር

መንገድነት ሽልማትን በተደጋጋሚ ማሸነፉም ስምና ዝናው ገናና እንደሆነ ማሳያ ነው። ሽልማቱን ከሰጡት ውስጥ በብሪታኒያ አየር መንገዱ የራሱ የአውሮፕላን አብራሪዎች የበረራ አስተናጋጅ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ያለው ሲሆን ዓለም አቀፍ ደረጃውን ያሟላና ለአፍሪካ አገሮችና ለሌሎችም ጭምር ሥልጠና በመስጠት በማስመረቅ የሚታወቅ ነው። ለግል አብራሪና ለንግድ አውሮፕላን አብራሪ ፈቃድ በመስጠት የአገርና የውጪ ዜጎችን በማሠልጠን ከአርባ ዓመታት በላይ የቆየ ልምድ አለው። ለብዙ የአፍሪካ አገሮች ብሔራዊ አየር መንገዶች እና ለግል አውሮፕላን ባለንብረቶች የአውሮፕላን ጥገና በማካሄድም የሚሠራ ተቋም ነው።

ከቦይንግ አውሮፕላን አምራች ኩባንያ ጋር ከ60 ዓመታት በላይ የዘለቀ የንግድ ግንኙነት ያለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ ለመንገደኞች አገልግሎት ቦይንግ 787 (Boeing 787 Dreamliner) አውሮፕላኖች በማዘዝና በአፍሪካ አገልግሎት ላይ በማዋል የመጀመሪያው ነው። ይህንንም የተረከበው ድሪምላይነር አውሮፕላን በነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ነበር። አየር መንገዱ ቦይንግ 777 ቦይንግ 787 ቦይንግ 737 በአጠቃላይ 68 እጅግ ዘመናዊ አውሮፕላኖችን ይጠቀም እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ።

በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1960ዎቹ D720 የመጀመሪያው ጄት ኤንጅን ያለው አውሮፕላን ወደ አፍሪካ ያመጣው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ ከዚያም ቦይንግ 707፣ 727፣737፣ 757፣ 767ን በማስመጣት ሲያገለገል ቆይቷል። ይህም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቦይንግ አንድ ምርት ውጭ ሁሉንም የቦይንግ አውሮፕላኖች እንደተጠቀመ ነው ሰነዶች

የሚያስረዱት። የኢትዮጵያ አየር መንገድ አሁንም ስም እና ዝናው እንደቀጠለ ነው።

### ንጉሥ ላሊበላ እና የገና በዓል

ስመ መንግሥታቸው ገብረመሥቀል፤ አንዳንድ ሰነዶች ላይ ደግሞ ገብረክርስቶስ ይባል። ይህ የ12ኛው ክፍለ ዘመን (1120 ዓ.ም) ታሪክ ነው። አጼ ላሊበላ በላስታ ላሊበላ ታኅሳስ 29 ቀን 1120 ዓ.ም እንደተወለዱ ታሪካቸው ያሳያል። እነሆ በዚሁ ቅዱስ ቦታ ላይ የገና በዓል በየዓመቱ ታኅሳስ 29 ቀን በድምቀት ይከበራል። ይህንኑ ምክንያት በማድረግ የዚህ ሳምንት አካል ስለሆነ ስለንጉሥ ላሊበላ ታሪክ ጥቂት እንቃኝ።

የዛግዌ ሥርዎ መንግሥት ንጉሥ ነበሩ። ለ40 ዓመታት ያህል በንጉሥነት የቆዩ ሲሆን ታሪካቸው ከ12ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ይዘልቃል።

የንጉሥ ላሊበላ ታሪክ በዋናነት የሚታወቀው የዓለም ሀብት በሆነው የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናት ነው። ከባለቤታቸው እቴጌ መስቀል ክብራ ጋር በመሆን 11 ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን አሰርተዋል። እነዚህም፤ ቤተ መዲሃኒያለም፣ ቤተ ማርያም፣ ጎለጎታ ሚካኤል፣ ኪዳነ ምህረት፣ ሥላሴ፣ ቤተ አማኑኤል፣ ቤተ ሊባኖስ፣ ቤተ ገብርኤል፣ ቤተ መርቆሬስ፣ ቤተ ጊዮርጊስ እና ቤተ መስቀል ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ቤተ ጊዮርጊስ በመስቀል ቅርጽ የተሰራ ነው።

ስለ አጼ(ንጉሥ) ላሊበላ ይህ ታሪክ ይነገራል። ንጉሡ ላሊበላ የሚለውን ስም ያገኘው፣ ሲወለድ በንቦች ስለተከበበ ነው ይባላል። ላል ማለት በአገውኛ ማር ማለት ሲሆን፤ ላሊበላ ማለትም ላል ይበላል (ማር ይበላል) ማለት እንደሆነ ይነግራል። ውቅር ቤተ ክርስቲያናቱን ንጉሡ ጠርቦ የሰራቸው ከመላዕክት እገዛ ጋር እንደሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ይነግራል።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓዊ ተጓዥ ላሊበላን ተመልክቶ «ያየሁትን ብናገር ማንም እንደኔ ካላየ በፍጹም አያምነኝም» ሲል ተናግሮ ነበር።

ቅዱስ ላሊበላ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ሕንጻዎችን ለመገንባት አሰበ፤ ከዚያም በጊዜው ከነበሩት አባቶች በተለይ ቀይት ከምትባል ባለአባት የጠየቀውን 40 ጊደር ለመግዛት በሚያስችለው ወርቅ ቦታውን ገዝቶ በከርሰ ምድር ውስጥ ያሉትን ሕንጻዎቹ ሊያወጣ ተዘጋጅ። ቅዱስ ላሊበላ የሚገነባባቸውን መሳሪያዎችለ 10 አመታት አዘጋጅቶ፤ በ1157 ዓ.ም ነግሶ በ1166 ዓ.ም ሕንጻውን ገንብቶ ጨረሰ። ቅዱስ ላሊበላ ከ40 ዓመታት የንግስና ዘመን በኋላ በተወለደ በ97 ዓመቱ ሰኔ12 ቀን 1217 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

# የዝነኞች ገጽ

# የአምባሰሏ ንግስት - ማሪቱ ለገሰ

**አቤል ገ/ኪዳን**

የአምባሰሏ ንግስት ታላቋ ድምጻዊት ማሪቱ ለገሰ በያዝነው ሳምንት ከሩብ ክፍለ ዘመን የአሜሪካ ቆይታ በኋላ ሀገሯ ገብታለች።አዲስ አበባ ስትገባም በርካታ አድናቂዎቿ ደማቅ አቀባበል አድርገውላታል።አስደናቂ ከሆነው የሙዚቃ ህይወቷ አንጻር ለማሪቱ የተደረገላት አቀባበል ቢያንስባት እንጂ አይበዛባትም።ለመሆኑ ግን ማሪቱ ለገሰ ማን ናት?

የክብር ዶ/ር አርቲስት ማሪቱ ለገሰ በደቡብ ወሎ ዞን በደሴ ዙሪያ ወረዳ ከድጅ 018 ቀበሌ አባባሌ መንደር በ1937 ዓ.ም ነው የተወለደችው። ገና ከልጅነቷ ጀምሮ ሙዚቃ የእሷ ልዩ ተሰጥኦ ነበር።በ1992 ዓ.ም ወደ አሜሪካ ከመውጣቷ በፊት ከጋዜጠኛ ደረጄ ሀይሌ ጋር ባደረገቸው ቃለመጠይቅ በልጅነቷ ዘፈን ባለበት ቦታ በሙሉ እየተጠራች ትዘፍን እንደነበር ተናግራለች።በሰርጉም በበአሉም ብቻ ዘፈን እና ጨዋታ ባለበት ቦታ ሁሉ እኔ አለሁ ትላለች ማሪቱ።ማሪቱ ከልጅነት ጀምሮ ወደ ደሴ ከተማ በመግባት በተለያዩ መጠጥ ቤቶች በግል ስትጫወት የቆየች ሲሆን በ1961 ዓ.ም የወሎ የአገር ባህል ተጫዋች ማህበር በ61 አባላት ሲመሠረት እርሷም የዚህ ማህበር አባል ነበረች።

በኋላ ላይ ደግሞ ዝነኛው ላሊበላ ኪነት ሲቋቋም ከመስራቾቹ ቀዳሚዋ ማሪቱ ነበረች።በወቅቱ ታዋቂው ከያኒ ቀለመወርቅ ደበበ ላሊበላ ኪነትን ሊያደራጁ ወደ ደሴ ሲሄዱ መጀመሪያ ከመረጧቸው አርቲስቶች መሀከል ዋናዋ ማሪቱ ናት።ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በወሎ ላሊበላ የኪነት ቡድን ውስጥ በመሆን በአምባሰል፣ አንቺ ሆዬ፣ በባቲ፣ በትዝታ ሙዚቃዎች ንግስት ሆና አገልግላለች።

ማሪቱ በዚያ ኪነት ውስጥ መሰንቆ ተጫዋች ከነበሩት ባለቤቷ እና ከሌሎች አርቲስቶች ጋር ብዙ ስራዎችን የሰራች ሲሆን በአንድ ወቅት ኮሎኔል መንግስቱ ሀይለማርያም ወደ ደሴ በሄዱበት ወቅት በኪነቱ እንቅስቃሴ ተደስተው ለቡድኑ አውቶቢስ ሸልመውት ነበር። ያ ወቅት ዛሬ እንደ ህዝብ መዝሙር የሚዘፈኑት እነ አምባሰል ፤ እሪኩም ፤ ከመከም ፤ ቃሮዬ ፤ አካሌ ውቤ ፤ ዞማዬ ለኢትዮጵያ ህዝብ በማሪቱ አንደበት የተበረከቱበት ወቅት ነበር።ዘፈኖቹ በጣም ከመወደዳቸው የተነሳ በየቦታው ይደመጡም ነበር።

በአንድ ወቅት አባቷ ከሚኖሩበት ገጠር ልጃቸውን ለማየት ወደ ደሴ ሲመጡ በህዝብ ማመላለሻ አውቶቢስ ላይ የልጃቸውን ድምጽ ይሰማሉ።ይሄኔ ሮጠው አውቶቢሱን ያስቆማሉ።ምነው ሲባሉ ይቺ የምትዘፍነው የኔ ልጅ ናት አባትሽ ሊጎበኝሽ መጥቷል ነይ ውረጅ በላት ይላሉ ፤ ሹፌሩም ስቆ የሚዘፍነው ካሴት እንደሆነ ሲነግራቸው በል ዘፍና እስክትጨርስ እዚሁ ቁምልኝ ብለው ተሳፋሪውን ሁሉ አስቀዋል።

ደሴ ላይ የራሷ የባህል ቤት የነበራት ማሪቱ አዲስ አበባ ከመጣች በኋላም ያንኑ ስራ እየሰራች ስኬታማ ሆና በህዝብም ተወዳጅ ሆና ነበር።ከሌሎች ታላላቅ አርቲስቶች ጋር በመሆንም በህዝብ ለህዝብ ስራ ላይ ተሳትፋለች።ከዚህም ጋር የተያያዘ ገጠመኝ አላት።ገጠመኙም እሷና ብዙነሽ በቀለ አሜሪካ ከደረሱ በኋላ አንድ ክፍል ይመደቡና ወደ ማረፊቸው ይገባሉ።ሲገቡም ክፍሉ ባዶ ሆኖ ያዩታል።እንዳይጠይቁ የቋንቋ እጥረት አለባቸው ፤ ዝም እንዳይሉም ሳይተኙ ሊያድሩ ሆነ።እንዲያው ቆመው ሲቆዝሙ የቡድኑ መሪ ካሳ ከበደ መጡ።ምን ሆናችሁ ነው ሲሏቸው ችግሩን ነገሯቸው።እሳቸውም ስቀው ማብሪያ ማጥፊያውን ሲጫኑት አልጋው ተዘረጋ።ማሪቱ እና ብዙዬም እንቅልፋቸውን ተኝተው አደሩ።

ማሪቱ የሰውም ሙዚቃ ደግሞ መዝፈን እና ልብስን ደግሞ መልበስ አትወድም።በተለይም በሀገር ባህል ልብስ ተጠቃሚነቷ ትታወቃለች።በመቶዎች የሚቆጠር የሀገር ባህል ልብስ እንዳለት ትናገራለች።በልጅ ሞት ሀዘን የደጋገማት ማሪቱ ሀገር ቤት ስትገባ የጠበቃት አቀባበል ግን አሁንም ብዙዎች እሷን እንደ እናታቸው እንደሚያዩአት ያመላከተ ነበር።ማሪቱ ወዳጇ ብዙ ነው።ከወዳጆቿ መሀከል ደራሲ አሌክስ አብርሀም አንዱ ነው።አሌክስ በአንድ ወቅት ስለ ማሪቱ የጻፈውን ግሩም ጽሁፍ እዚህ ጋር እንጨምረው።

ማሪቱ ለገሰ ዘፋኝ ናት እንዴ ?

"የአንድ ጓደኛየ እናት ይሞታሉ .... ቆይቷል ... ለቀስተኛው ድንኳኑን ሞልቶ እስኪወጣለት አልቅሶ ለቅሶም



ቀዝቀዝ እያለ ...ወደሰባተኛው ቀን አካባቢ ሁኖታል .... ዘግይቶ የመጣ ወዳጅ ዘመድ አልፎ አልፎ እያለቀሰ ሲገባ ብቻ ውስጥ ያለው ቤተሰብ ተቀብሎ ትንሽ ማልቀስና ተው ተው ተብሎ ዝም ማለት ካልሆነ በስተቀር .... ለቅሶው ወደማብቃቱ ነበር ! ታዲያ ወደአስር ሰአት ገደማ ይሆናል ከድንኳን ውጭ እንደቤተክርስቲያን ደውል የሚያስገመግም መረዋ ድምፅ አንጀት በሚበላ ዜማ ሙሾውን እያወረደ ወደድንኳኑ ቀረበ ....ለስራ አዲስ አበባ ከርማ ገና ወደደሴ የገባችውና መርዶውን ሰምታ እህል ውሃ ሳትል የመጣቸው የሟች ቅርብ ወዳጅ ማሪቱ ለገሰ ነበች እንግዲህ አልቃሸዋ... መንደርተኛው በዚች ሴት የሃዘን እንጉርጉሮ ልቡ ተነካ ... እንኳን ቤተሰብ ሊያፅናና ሁሉም የየራሱን ብሶት ዘርግፎት ትኩስ ሞት አስመሰለው .... እስካሁን ያ ድምፅ ውስጤ አለ ...!

የገረመኝ ይሄ አይደለም ...ከወራት በኋላ የቀለጠ ሰርግ ላይ ማሪቱን እንደማንኛውም ታዳሚ ተጠርታ ተገኝታለች ....«ማሬዋ አቦ እንደው ለሙሽሮቹ ክብር » ተብላ ማሲንቆ የያዘ ሰውየ አጅቧት ያ ተአምረኛ ድምፅ ዳሱን ሞላው ....ጫጫታው ባንዴ መርፌ ቢወድቅ ወደሚያሰማ ዝምታ ተቀየረ ... ረጭጭ .... የማሪቱ ድምፅ ይሄው በእያንዳንዱ ኢትዮጲያዊ ደም ስር ውስጥ ዛሬም አለ ... ያኔም ይነዝረን ጀመረ... የማሪቱ አምባሰል የሰርገኛውን መንፈስ ወሰደው .... እናም ማሪቱ የሰርግ ዘፈን አልነበረም በአንባሰል ዜማዋ ያንቆረቆረችው ...ድብን ያለ የሃዘን እንጉርጉሮ እንጅ ....እየዘፈነች ከወራት በፊት እናታቸውን በሞት ወዳጡት ቤተሰቦች ሄደች ...የሟች ሴት ልጅና የልጅቱ አባት ... ማለትም የሟች ባለቤት ....

ልጅቱም ጥቁር ጥለት ያለው ነጠላ ለብሳ ...አባትየውም ጥቁር ቆብ አድርገው ጥጋቸውን ይዘው ተቀምጠው ነበር ....ሰርገኛው መሃል ....ማሪቱ በሚያስደምም የአምባሰል ዜማዋ ... አሁን ላይ የረሳሁትን ግጥም ብቻ ሃዘን ምናባቱ ... ሟችም አፈር ይቅለላት የሚሉ ቃላት ያሉበት ....እያቀነቀነች ወደልጅቱ ቀረበች እናም ጥቁር ጥለት ያለው ነጠላዋን ከልጅቱ ላይ ገፋ የራሷን ባለ ባንዲራ ጥለት ነጠላ ልጅቱ ላይ ደረበችላት (እንግዲህ በዚህ ሁሉ ዘፈኑ አልተቋረጠም) ሌላ ሰውየም የአባትየውን ጥቁር ቆብ አወለቀ .... ከየት እንዳመጡት እንጃ ሃዘንተኛውን ልጅ ፀጉሯን ቅቤ ቀቡት ...አባትየውንም ለወጉ ፀጉራቸውን በቅቤ ሸው ደረጓቸው መስሎኛል ....... ሰርገኛው እልልታውን አቀለጠው ......ግዲህ በወሎ ባህል ሃዘን በቃ የሚለው ጎረቤት ነው ....ሃዘንተኛው ከዛ በኋላ ጥቁር አይለብስም ራሱንም አይጥልም ! ማሪቱ ወዲያው ዜማውን ቀየረችው ሞቅ ያለ የቦረና ዜማ ....ከዛማ ምኑ ቅጡ ሰርግ ቤቱ በጭፈራና በእልልታ በአንድ እግሩ ቆመ !

ማሪቱ ለዎሎ ህዝብ ዘፋኝ አይደለችም!! በዘፈኗ ኑሮውን ብሶቱን ፍልስፍናውን ባህሉን ፍቅሩን ማንነቱን የከተበች ህያው ብራና እንጅ ....ማሪቱ ለገሰ ለመላው የኢትዮጲያ ህዝብ እነዛን ድንቅ ቅኝቶች ሳይዛነፉ ተፈጥሯዊ ለዛቸውን እንደያዙ በድምፅ ያቆየች የታሪክ ብራና ናት ....ማሪቱ ዘፋኝ አይደለችም .... እራሷ ዜማ ናት ... ማሪቱ ብትጠና የማታልቅ እራሷ ትውፊት ናት ራሷ ባህል ናት ! እውነቱን እናውራ አይደል ....አንድ ሰው የትም ሳይወጣ ሳይወርድ ቁጭ ብሎ የማሪቱን ዘፈን ያድምጥ ዘፈን ሳይሆን የህዝቡን ደስታ ... የህዝቡን ብሶት ...የህዝቡን መከራ የህዝቡን ክፉና ደግ ዘመኖች ሁሉ መሃተም በሆነ ድምፅ ልቦናው ላይ ያትማል !

ማሪቱ ምናለች ...

ውሸቴን ነው እንጅ እንደው ስግደረደር
እኔስ ለዎሎ ልጅ ውሃ ሸጨ ልደር
እኔስ ለጦቢያ ልጅ ውሃ ሸጨ ልደር ....

ያኔ በዛ ዘመን በወሎም ይሁን በመላው ኢትዮጲያ እንኳን ውሃ ወተት መሸጥ ነውር ነበር ...እግር የጣለው ሰው ፎሌ ሙሉ ርጎውን ግፎና አንጀቱን አርሶ መርቆ ብቻ የሚሄድበት ዘመን .... ታዲያ «ውሃ ሻጭ » ማለት ትልቅ ፀያፍ ስድብ ነበር ... ማሪቱ ይሄን ነው የምትነግረን «ለአገሬ ልጆች ስል ፀያፍ ልባል ምናምንቴ ልባል » አለች ! ስለህዝብ ስድብን ልሸከም አለች ! ስለአገር አንድነት ... ተከባብሮ ተፋቅሮ ስለመኖር በዘፈኖቿ ብዙ ብዙ ብላለች ...ጀግንነታችንን «ዘራፍ » ብላ የማይወርድበት ማማ ላይ ሰቅለዋለች ! ያውም ህዝቡ ውስጥ እንደህዝቡ እየኖረች ... በእግሯ የስንት ሰአት የእግር መንገድ እየተጓዘች ....ግጥም ተፅፎላት ዜማ ተቀምሮላት በይ ተብላ ሳይሆን ....ድምፅ ተሸጦ ግጥም ተሸቅጦ በማይኖርበት እንደውም መዝፈን «አዝማሪ» እያስባለ በህዝብ አስነቅሮ በሚያስተፋበት ዘመን ....ማሪቱ ለገሰ ፊደል ሳትቆጥር የአንድን ህዝብ እውነት በድምፅ ብራናዋ ላይ ቀርፃ ለትውልድ አኖረችው ... !

ያኔ እንደዛሬው የሙዚቃ ተንታኝ ባልነበረበት ዘመን በህዝቡ ልቦና ተመዝና ሚዛን የደፋች በተፈጥሮ ዜማን አብጠርጥረው በሚያውቁ አባቶቻችን መንፈስ ላይ ሃሴትን የዘራች ታላቅ ሴት ናት ማሪቱ ለገሰ!! ...ያውም ሴት ልጅ አደባባይ ወጥታ ልትዘፍን ቀርቶ ቀና ብላ የባሏን አይን እያየች መናገሯ እንደብልግና በሚቆጠርበት ዘመን ነው የምላችሁ ! ሬዲዮው የሚነግረን እነሜሪ አርሜዲ ቀድመው አደባባይ ወጡ እያለ ነው አይደል ...ዘጋቢ በሌለበት ታሪኳን በድምፅና ምስል ቀርፆ የጮኸ ሰው በሌለበት ሆነ እንጅ .... ያውም በድቅድቅ ጨለማ በባዶ እግሯ ስለዘፈን ጭው ካለ ገጠር ተሰዳ ከተማ የተከሰተች ሴት ጥራ ካላችሁኝ ቅድሚያ ማሪቱን ከመጥቀስ ወደኋላ አልልም .... ሙዚቃ ትውፊታችን ነው ...ባህላችን ነው ካልን ከዚች ሴት በላይ የዘመኗን እውነት ዘመን በማይሽረው ዜማና ግጥም ያስቀመጠ ኢትዮጲያዊ ዘፋኝ ካለ ይሄው አምጡና ሚዛኑ ላይ አስቀምጡ !

ማሪቱ ለገሰ እንደታዋቂ እራሷን ላይ ሰቅላ በህዝቧና በራሷ መካከል የክብር አጥር የገነባች ሴት አልነበረችም ...እንደውም ደሴ በነበረችበት ቀን ሰው ሞተበት ሲባል ነጠላዋን አዘቅዝቃ የእዝን ሻይና ዳቦ ይዛ ሃዘን ቤት ስትሄድ መንገድ ላይ ታገኙዋት ነበር ...ይች ሴት እንዲህ በታላላቆቹ የሙዚቃ ሰዎች እንኳን የተመሰከረለትን ድምፅዋን ሳንቲም መሰብሰቢያ አላደረገችውም ...እንዳላት ስምና ዝና ምንም ነገር አልነበራትም ... አሁን ኑሮዋ በውጭ አገር ነው እንደምሰማው ግን እዛም ይሄ ነው የሚባል ሃብት ያፈራች ሴት አይደለችም ... ይታያችሁ ልክ በሩጫው ለአስርት አመታት የክቡር ዶክተር አትሌት ሃይለ ገብረ ስላሴ ብቃቱ ሳይወርድ በሩጫው እንዳኮራን ...ማሪቱ ለገሰ በትንሹ ከአርባ አመታት በላይ የድምፅዋ ለዛ እንዳለ ብቃቷ ትንሽ እንኳን ሳይወርድ ዛሬም እያስደመመችን አለች ! እኔ ሳልወለድ የዘፈነችውን ዘፈን ስሙና ከሳምንት በፊት የዘፈነችውን ዘፈን አድምጡ ከዛ ያልኩት እንዳልተጋነነ ይገባችኋል !

አምባሰልን ከማሪቱ ለገሰ በላይ ያሽሞነሞነው ድምፃዊ ካለ ...ይሄው እከሌ አለ በሉና ጥሩ ...ሰርፀ ፍሬስብሃት አንዴ ምናለ «ስለማሪቱ የአዘፋፈን ስልትና የድምፅ ቅላፄ እንደው ተአምር ነው ከማለት ውጭ የምለው የለም ...» አለ ....እኔም ዛሬ ስለተአምረኛዋ ማሪቱ ለገሰ አወራኋችሁ "

# ዓለም አቀፍ

## ፕሬዚዳንቱን የሚያሳይ ያልተገባ ቪዲዮ ለቀዋል የተባሉት 6 የደቡብ ሱዳን ጋዜጠኞች ታሰሩ

የደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ሱሪያቸው ረጥቦ የሚያሳይ ቪዲዮ ተጠቅሟል የተባሉት 6 የደቡብ ሱዳን ጋዜጠኞች በጸጥታ ኃይሎች መታሰራቸው የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ኮሚቴ (ሲፒጄ) ገለጸ።ያልተገባ የፕሬዚዳንቱን ቪዲዮ አሳይተዋል በሚል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉት ጋዜጠኞች በደቡብ ሱዳን የሚተዳደረው የደቡብ ሱዳን ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኤስኤስቢሲ) ሰራተኞች መሆናቸውም ነው የተገለጸው።



ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር

ሲፒጄ የሚዲያ ዘገባዎችን እና ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ ሰዎችን ጠቅሶ እንደገለጸው ከሆነ፤ እስረኞቹን የቴክኒክ ክፍል ዳይሬክተር ጆቫል ቶምቤ፣ የካሜራ ኦፕሬተርና ቴክኒሻን ቪክቶር ላዶ፣ የካሜራ ኦፕሬተሮች ጆሴፍ ኦሊቨር እና ጃኮብ ቤንጃሚን፣ የካሜራ ኦፕሬተርና ቴክኒሻን ሙስጠፋ ኦስማን እንዲሁም የቁጥጥር ክፍል ቴክኒሻን ቸርቤት ሩበን የተባሉ ባለሙያዎች ናቸው።

የሲፒጄ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ተወካይ ሙቶኪ ሙሞ እስሩ በዘፈቀደ የተደረገው የእስር ዘመቻ ተገቢ እንዳልሆነ ተናግረዋል።"ባለስልጣናት እነዚህን ስድስት የኤስኤስቢሲ ሰራተኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መልቀቅና ያለ ተጨማሪ ማስፈራራት እና የእስር ማስፈራሪያ መስራት እንደሚችሉ ማረጋገጥ አለባቸው"ም ብለዋል ሙሞ።

በተንቀሳቃሽ ምስል (ቪዲዮ) ምክንያት ጋዜጠኞች እንደታሰሩ የሚገልጸውን ዘገባ በመጀመሪያ ውድቅ ያደረገው የደቡብ ሱዳን የጋዜጠኞች ህብረት (UJOSS) በበኩሉ ምርመራው በፍጥነት እንዲጠናቀቅ ጠይቋል።"በመጀመሪያ ደረጃ የባለሙያ ጥፋት ወይም ጥፋት ካለ ባለስልጣናቱ ጉዳዩን በፍትሃዊ፣ ግልጽ በሆነ እና በሕጉ መሰረት ለመፍታት አስተዳደራዊ ወይም ሕጋዊ ሂደትን ያፋጥኑ" ሲልም ጠይቋል ህብረቱ።

የሱዳን ፖስት ገለልተኛ የዜና ድረ-ገጽ ማንነታቸው የማይታወቅ የመንግስት ቴሌቪዥን ሰራተኛን በመጥቀስ እንደዘገበው፤ ፖሊስ የኪርን ሽንታቸውን ሲለቁ የሚመስል ክስተት የቀረጸው ጋዜጠኛን ሲፈልግ ቆይቷል። የሱዳን የጸጥታ ኃይሎች የጠረጠሯቸው ጋዜጠኞች በቁጥጥር ስር ቢያውሉም፤ አንድ የኤስኤስቢሲ ባለስልጣን ታማዙጅ ለተባለ ሬድዮ በሰጡት መረጃ፤ የቴሌቭዥን ጣቢያው የተባለውን የሳልቫ ኪር ምስል አየር ላይ እንዳልዋለ ተናግረዋል።

አሁን ላይ ለጋዜጠኞቹ እስር ምክንያት የሆነው ተንቀሳቃሽ ምስሉ ባለፈው ወር በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በሰፊው ሲሰራጭ እንደነበር አይዘነጋም።ይህም የ71 ዓመቱ ፕሬዚዳንት የጤና ሁኔታ እና ከግጭት፣ ከረሃብ እና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የምትታገል ሀገርን ለማስተዳደር ብቃት ላይ ጥያቄዎችን አስነስቷል።

በሌላ በኩል በማህበራዊ ሚዲያ ላይ እንደዚህ ያሉ ምስሎችን በመለጠፍ ስነ ምግባር ላይ እና ለሽማግሌው ያለ ርህራሄ ማጣት ላይ ከባድ ክርክር አስነስቷል።ሳል-ቫኪር እንደፈረንጆቹ ከ2011 ጀምሮ ደቡብ ሱዳንን እየመሩ ቢሆንም በሀገሪቱ የሚስተዋለው የፖለቲካ ቀውስ የሀገሪቱን ሰላም በዘላቂነት ለማረጋገጥ ማነቆ እንደሆነ ይነገራል።

ለድርድር ዓመታት የፈጀባቸው የደቡብ ሱዳን ፖለቲከኞች በመጨረሻም በ2024 ምርጫ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ፍኖተ ካርታ አዘጋጅተው የሀገሪቱን መጻኢ እድል ለመወሰን ከስምምነት የደረሱት በቅርቡ እንደነበርም አይዘነጋም ሲል የአል ዐይን ዘገባ ያመለክታል።



## አሜሪካ በኢራን ድሮን አምራች ኩባንያ ላይ ያነጣጠረ አዲስ ማእቀብ ጣለች

ኢራን ለሩሲያ ድሮን በማቅረቧ ምክንያት አሜሪካ አዲስ ማእቀብ ጥላባታለች፡፡ አሜሪካ እንደገለጸችው ኢራን ለሩሲያ የምትሰጣቸው ድሮኖች በዩክሬን ውስጥ ያሉ የሰላማዊ ሰዎችን መሰረተ ልማት ለማውደም ጥቅም ላይ ውለዋል ተብሏል፡፡ በዚህ ምክንያት አሜሪካ የኢራን ሰው አልባ አውሮፕላኖች አቅርቦት ላይ ያነጣጠረ አዲስ ማዕቀብ አርብ ዕለት መጣሏን አስታውቃለች፡፡

ሩሲያ ከጥቅምት ወር ጀምሮ ወሳኝ በሆኑ የዩክሬን መሠረተ ልማት አውታሮች በሚሳይል እና ሰው አልባ አውሮፕላኖች ጥቃት ስትሰነዝር ቆይታለች። የአሜሪካ የግምጃ ቤት ዲፓርትመንት የኢራን ኪዮድስ አቪዬሽን ኢንዱስትሪዎች (QAI) እና ቀላል አውሮፕላኖች ዲዛይን እና ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በመባል በሚታወቁት ስድስት ስራ አስፈፃሚዎች እና የቦርድ አባላት ላይ ማዕቀብ ተጥሏል ብሏል።

ከፈረንጆቹ 2013 ጀምሮ በአሜሪካ ማዕቀብ ስር የሚገኘውን ኪዮድስ አቪዬሽን ኢንዱስትሪዎች ሰው አልባ አውሮፕላኖችን የመንደፍ እና የማምረት ኃላፊነት ያለው የኢራን የመከላከያ አምራች እንደሆነ ግምጃ ቤቱ ገልጿል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን
Ethiopian Intellectual Property Authority

ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ጋር
በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም

## የኢትዮጵያ የቅጅ መብት ሕግ

በብሩክ ወርቅነህ

በጎርጎሮሳውያን ዘመን አቆጣጠር አዲስ አመት በሚከበርበት ዕለት (ጥር /January 1) የቅጅ መብት ሕግ ቀን ታስቦ ይውላል። ከሰሞኑም የ2023 የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት በተከበረበት ዕለት ልክ እንደወትሮው የቅጅ መብት ሕግ ቀን ታስቦ ውሏል። ውድ አንባብያን፤ ይህንን አስመልክቶ በዛሬው ትምህርታዊ ጽሁፋችን የኢትዮጵያን የቅጅ መብት ሕግ አንዳንድ ነጥቦችን ለግንዛቤ ይረዳቹህ ዘንድ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

የአእምሯዊ ንብረት መብቶች እንደ ፈጠራ ሥራዎቹ ባህሪ በተለያየ መንገድ የሚጠበቁ ሲሆን በዋናነት በፓተንት፣ በንግድ ምልክትና በቅጅ መብት ይጠበቃሉ። የስነጽሁፍ፣ የኪነጥበብ፣ የስነጥበብ እና የኮምፒውተር ፕሮግራም የመሳሰሉት የፈጠራ ሥራዎች የሚያስገኙት መብት በቅጅና ተዛማጅ መብት አዋጅ ይጠበቃሉ። በሀገራችን የቅጅና ተዛማጅ መብትን ጥበቃ ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንድ የፈጠራ ሥራ አዲስ ከሆነ እና ግዝፈት ካገኘ (ሊነበብ ወይም ሊደመጥ አልያም ሊታይ በሚችል መልኩ ተዘጋጅቶ ሥራው ከተጠናቀቀ) ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የቅጅ መብት እንደሚያገኝና ጥበቃ እንደሚደረግለት ይደነግጋል። የቅጅ መብትን መሰረት አድርገው የሚመነጩ ተዛማጅ መብቶችም ጥበቃ ይደረግላቸዋል። የኢኮኖሚና የሞራል መብቶችን በመዘርዘር ያጎናጽፋል። የቅጅ መብት ሥራውን በመሥራት ብቻ የሚገኝ ግለሰባዊ መብት ነው። የቅጅ መብት ያለምዝገባ የሚገኝ መብት ነው።

### የፈቃደኝነት የቅጅና ተዛማጅ መብት ምዝገባ

በቅጅ መብት ኢንደስትሪው ላይ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ከሚያስችሉ ዘዴዎች መካከል አንዱ የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎችን መመዝገብና የባለቤትነት ማስረጃ መስጠት ነው። በመሆኑም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአዋጅ አንቀጽ 39 ቁ. 1 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ህጋዊ የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎችን መመዝገብና የባለቤትነት ማስረጃ መስጠት የሚያስችል ደንብ ቁጥር 305/2006 ዓ.ም ደንግጓል። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን አገልግሎቱን በመስጠት ላይ ይገኛል።

የቅጅ መብት ምዝገባ በመብት ባለቤት ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ አገልግሎት ነው። ከላይ እንደተገለጸው የቅጅ መብት አዲስና ግዙፍነት ያገኘ የፈጠራ ሥራን በመሥራት የሚገኝ በመሆኑ መመዝገብ የቅጅ መብት አያስገኝም፤ አለመመዝገብም የቅጅ መብት አያሳጣም። ነገር ግን መመዝገብ ቀዳሚ የመብት የባለቤትነት ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) ያስገኛል።

### የቅጅና ተዛማጅ መብት ምዝገባ የምስክር ወረቀት

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 77 መሰረት የኮፒራይት ተግባራት የፌዴራል መንግሥት ስልጣን በመሆኑ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን የሚሰጠው የምዝገባ ምስክር ወረቀት ብቸኛ በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ነው። የቅጅ መብት የምዝገባ ምስክር ወረቀት በአዋጁ የተሰጡትን የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ለመጠበቅና የመብት ጥሰትን ለመከላከል አብይ ድርሻ አለው። የመብት ዝውውርን እንዲሁም የንግድ እንቅስቃሴን ሕጋዊ በሆነ መልኩ ለማቀላጠፍ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። በፍርድ ቤት የሚደረጉ የመብት ማስከበር ክርክሮች ላይ ቀዳሚ የባለቤትነት ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል።

የቅጅ መብት ምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚያገለግለው ለአምስት አመት ብቻ ነው። ከዚያ በላይ አገልግሎት እንዲኖረው ከተፈለገ በየአምስት አመቱ በባለቤቱ ፈቃድ መታደስ አለበት። ሌላው የቅጅ መብት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት በአመልካች ቃለ መሃላ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ማስረጃ ነው። ይህ የምስክር ወረቀት በሃሰት ቃለ መሃላ ላይ ተመስርቶ የተሰጠ መሆኑን በሌላ ህጋዊ ማስረጃ ከተረጋገጠ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል።

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል!
መልካም የገና በዓል ይሁንልዎ !
የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፅሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ከብርሀነ ልደቱ አድማስ ባሻገር

ገና ወይም በዓለ ልደት አልያም ብርሀነ ልደት በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በየአመቱ ታህሳስ 29 ፤ በየአራት አመቱ ደግሞ ታህሳስ 28 ቀን የሚከበር ሀይማኖታዊና ባህላዊ በዓል ነው ፡፡ ገና እየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ዘር ሁሉ ለማዳን ከሰማይ ሰማያት ወርዶ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማሪያም በበጎች ግርግም የተወለደበት ልደት የሚዘከርበት ዕለት ነው ፡፡ ለዚህ ነው የበዓላት ሁሉ በዓል ተደርጎ የሚወሰደው ፡፡ የገና ስረወ_ ቃል ( መነሻ )የበዓሉ ሁሉ ንጉስ ፤ ታላቅና ገናናነት ከሚገልጸው “ ገናና “ ከሚለው ቃል የሚመዘዝ ነው፡፡ እየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ ቤተልሔም ሲወለደ ከነገስታቱና ከመሳፍንቱ ከእነ ሔሮድሰ ተሰውሮ ለእረኞች ተገልጧል ፡፡

እረኞችም ከመልዓክት ጋር “ ስብሀት ለእግዚአብሔር በሰማያት ...” ሲሉ ለክብሩ ዘምረዋል፡፡ አዋቂዎቹ ሰብዓ ሰገሎች የከበረ ስጦታ ይዘው በቤተመንግስት ሲፈልጉት በበጎች ግርግም ነበር የተገኘው ፡፡ እነዚህ ተምሳሌቶች እየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ መካከል ቆሞ የነበረውን የጥል ግድግዳ ለማፍረስ ፤ እርቅን ሰላምን ለማውረድ መምጣቱን ያበስራል ፡፡

ገናን ለ2015 አመታት ጊዜ ስናከብረው ፍቅሩንና ሰላሙን ልብ አላልነውም ፡፡ አልኖርነውም ፡፡ ገናን ከቅርጫው ከዳቦው ፤ ከድግሱና ሽቀጥ ከመሰጣጣት ባሻገር የልደቱን አብይ አላማ አልኖርነውም ፡፡ በተለይ ካለፉት አራት አመታት ወዲህ በሀገራችን የተከሰተው ቀውስ ፤ ጭፍጨፋና የመረረ ጥላቻ ይሄን የሚያረጋግጥ ነው ፡፡ እስኪ በብርሀነ ልደቱ መስኮት የሌሎችን ባህላዊ ወረቶቻችን/ cultural capital/ አኳኋንና አከራረም እንቃኝ ፡፡

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚከበሩ መንፈሳዊና ባህላዊ ሁነቶች የተሸከሙትን ግዙፍ መልዕክቶችና አንድምታዎች አለፍ አለፍ ብለን እየተመልከትን ሐሳብ እናወራርድ ፡፡ፍቼ ጨምበለላ ፤ ቡሔ ፤ ሻደይ ፤ አሸንዳ፣ ሶለል አይነ ዋሬ ፤ እንቁጣጣሽ ፤ መስቀል ፤ መስቀላዮ ፤ ኢጋመ ፤ ጊፋታ ፤ ኢ ሬቻን ፤ ጋሮ ፤ ቺሜሪ ፤ ትንሳኤ፣ ወዘተ . በአንድም በሌላ በኩል በተለያዩ የሀገራችን ማህበረሰቦች የሚከበሩ ሀይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ክዋኔዎች ናቸው ፡፡

ሁሉም ማለት ይቻላል ተስፋን ፤ ፍቅርን ፤ ነፃነትን ፤ አብሮነትን ፤ አንድነትን ፤ ምስጋናን ፤ እርቅን ፤ ይቅርታን፣ እኩልነትን ፤ ወዘተረፈ . የሚያውጁ፣ የሚለፍፉና የሚሰብኩ ናቸው ፡፡ግን በነቂስ ወጥተን ለዘመናት በየአመቱ በአደባባይ የምናከብራቸው የምንዘክራቸውን ያህል በዕለት ተዕለት ኑሮአችን እንኖራቸውም ፡፡ እንለማመዳቸውም ፡፡

ይሁንና ከጊዜው ቀውሶች ፤ ፈተናዎች መውጣት ማገገምና ማንሰራራት የቻልነው በቀሩን ሽርፍራፊ እንጥፍጣፊ በባህላዊ ንብረቶቻችን social capital መሆኑን ልብ ይሏል ፡፡ ባለፉት 27/50 አመታት ቀን ከሌት ተቋማዊና መዋቅራዊ ሆኖ እንደ ተሰበከው ልዩነት፣ ጥላቻና ዘረኝነት ቢሆን ኑሮ እርስ በእርስ ተበላልተናል ፡ ተጨራርሰናል ፡፡ለዚህ ነው መዳኛችን ፤ ማገገሚያችንና ማንሰራሪያችን የሆነውን ባህላዊ ወረት ወደሙላቱ መመለስ ለነገ የሚባል ጉዳይ የማይሆነው ፡፡

ባህላዊ ወረታችን ለበጎ አላማ ሲውል ሀገርን ከጥፋት ከእልቂት እሳት እንደሚታደግ በጋሞ ሀገር ሽማግሌዎች ተመልክተናል ፡፡የጋሞ የሀገር ሽማግሌዎች እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ ለበቀል ተነስቶ የነበረውን የአርባ ምንጭና የአካባቢውን ወጣት ለምለም ሳር ይዘው ተንበርክከው በመለመን ቁጣውን አብርደው መልሰውታል ፡፡

ይህን የሀገር ሽማግሌዎች ገድል በጥሞና ለተረዳው የአርባ ምንጩን እሳት ብቻ አይደለም ያጠፉት የአርባ ምንጩን ጥፋት ተከትሎ በመላ ሀገሪቱ ሊዛመት የነበረውን የበቀል ሰደድ እሳት ጭምር እንጅ ፡፡ቁጣ አብራጁ ይህ የጋሞ አባቶች ልመና ( ጋሞ ወጋ ) እየጠፋ፣ ትኩረት እየተነፈገው ያለው ባህላዊ ወረታችን ተጠብቆ ለትውልድ ሲተላለፍ ሀገርን እንዴት ማዳን እንደሚችል ጥሩ ማሳያ ነው ፡፡

የጋሞ አባቶች ከአራት አመት በፊት ልዩ የበጎ ሰው ተሸላሚ መሆናቸው በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያለ አንዳንች ልዩነት ዳር እስከዳር አድናቆትን ተቀባይነትን ያተረፈው በዚህ እሳቤ ነው ፡፡ሕግን ለማስከበር ከምናደርገው ጅምር ጥረት ባልተናነሰ በየአካባቢው እንደ ጋሞ ወጋ አይነት የሽምግልና ፤ የእርቅ ባህላዊ ካፒታሎቻችንን ላይም መስራት ይጠበቅብናል ፡፡ከዚህ መሳ ለመሳ የአክራሪነት አዝማሚያ ፤ እኩይ አስተሳሰብ እንዲገታ ብሎም ተሸንፎ ከሰላምና ከእርቅ መንገድ ገለል፣ ዘወር እንዲል ድልብ የሆኑ የባህላዊ ንብረቶቻችን ወረቶች የማይተካ ሚና አላቸው ፡፡

ሁሉም ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ባህላዊ ወረቶች ባለፀጋ ስለሆኑ የየራሳቸውን መዋጮ ማበርከትና ወደ ስራ መግባት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በየአካባቢያችን፣ በየቀዬአችን የምናንፀው ፤ የምናቀነቅነው ከባቢያዊ ብሔርተኝነት ወደ አክራሪነት ፤ ፅንፈኝነት የሚያንደረድር ወደገደል አፋፍ የሚገፋ ስለሆነ እነዚህን ባህላዊ ወረቶች በመጠቀም መግታት ያስፈልጋል፡፡ የዜጎች ማንነት እሴት እንደተከበረ ወደ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት የሚያደርሰንን ቀና መንገድ በቅንነት መቀላቀል ፤ መያያዝ ይገባል ፡፡

ይህ ሀገራዊ ብሔርተኝነትም ከገደቡ ፤ ከውሃ ልኩ እንዳያልፍ ጥንቃቄ ማድረጉ እንዳለ ሆኖ ፡፡ አይደለም ዘውጌአዊ ፤ ወንዜአዊ ብሔርተኝነት ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት በአግባቡ ካልተያዘ ፤ የጎረቤቱን የሚጎመጅ ፤ የሚመኝ ፤ የሚመቀኝ ሆኖ የመውጣት አደጋ ስላለው በብልሀት ፤ በማስተዋል ሊቀነቀን ይገባል ፡፡ በዛድባሬ ይመራ የነበረው “ የታላቋ ሶማሊያ “ አክራሪ ብሔርተኝነት ለዚህ ጥሩ አብነት ነው ፡፡ የናዚው አዶልፍ ሒትለር የአርዓያም ዘር ልፋፊ ነቢብ በአለማችን ላይ ያስከተለው እልቂትና ቀውስም አይዘነጋም ፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ጥንታዊ መሆኗን የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ ፡፡ ከ3000 እስከ 8000 አመት የሚደርስ ታሪክ ባለጸጋ እንደሆነች የታመናል፡፡ ጥንታዊነቷ የዳበረ ሀገረ መንግስት ባለቤት አድርጓታል፡፡ የደለቡ ባህላዊ ወረቶች መናኸሪያም ናት ፡፡ ባህል ፤ ባህላዊ ንብረትስ ምንድን ነው የሚለውን ለመግባቢያ ያህል እንመለከታለን፡፡ ባህል ሁሉንም የሚያስማማ የሚያግባባ ወጥ የሆነ ትርጉም ብያኔ ባይኖረውም የአንድ ማህብረሰብ ወይም ሕዝብ ዕምነት፣ ልማድ፣ ወግ በኪነ ጥበብ እና በስነ ጥበብ ተዳውሮ ፤ ድርና ማግ ሆኖ ፤ ተሸምኖ፣ ተንሰላስሎ የመገኘት፣ የመገለጥ ዥጉርጉር ሕብራዊ ደማቅ ቀለም ነው ፡፡

በደስታ ፤ በሀዘን ፤ በስራ ፤ በሀይማኖት፣ በትምህርት፣ ወዘተ . የህይወት አንጓዎች ይገለጻል ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ባህልን :- የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፤ ወግ ፤ ልማድ፣ እምነት ፤ ...፡፡ በማለት ሲተረጉመው ፡፡ የደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በበኩሉ ባህል :- ልማድ፣ ደንብ ሲል ይፈታዋል ፡፡

ባህላዊ ንብረት ( cultural capital ) የሚለው ሀረግ ፔሬ ቦርዴው በተባለ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ የተነሳ የስነ ሕብረተሰብ ተመራማሪ እንደተፈጠረ የተለያዩ የዘርፉ ድርሳናት ያትታሉ፡፡ ባህላዊ ንብረት በማህበረሰብ ውስጥ ያለን ተቀባይነት ቦታ ከፍ ለማድረግ ዕውቀትን ፤ ፀባይና ክህሎትን የማሳደግ የማካበት ሂደት ነው ፡፡

ባህላዊ ንብረት በግለሰብ ፤ በማህበረሰብ ከፍ ሲልም በሕዝብ በሀገር ይሰላል፡፡ የበለፀገ ባህላዊ ንብረት ያካበተ ግለሰብ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ከፍ እንደሚያደርገው ሁሉ ያደገ የለማ ባህላዊ ንብረት ያለው ማህበረሰብ ሕዝብ በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍ ያለ ተቀባይነት ይኖረዋል ፡፡

ባህል ማለትም የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፤ ወግ፣ ልማድ ፤ እምነት ፤ ወዘተ . በሂደት በዕውቀትና በክህሎት እየበለፀገ ፤ እየዳበረ ሲሄድ ለሀገር ሰላም ፤ አንድነት ከፍ ሲልም እድገት የላቀ አስተዋጾ ይኖረዋል፡፡ በተቃራኒው ባህል በዕውቀት ፤ በክህሎት ካልበለፀገ አይደለም ለሀገር ሰላምና ዕድገት መዋል ይቅርና የማህበረሰቡን እሴቶች ጠብቆ ማቆየት ካለማስቻሉ ባሻገር የዕለት ተዕለት ችግሮችን እንኳ መፍታት የሚሳነው ይሆናል ፡፡

ባህላዊ ንብረት እንደ ኢኮኖሚያዊ ንብረት ማለትም ገንዘብ በአግባቡ ኢንቨስት ተደርጎ ሰላምን ፤ ፍቅርን፣ እርቅን ፤ መነጋገርን ፤ መቀባበልን ፤ መከባበርን፣ መተባበርን ፤ አንድነትን ፤ ወዘተ . እውን ማድረግ ካልተቻለ እንደባከነ እንደከሰረ ሊቆጠር ይችላል ፡፡

ሀገርን ሕዝብን ከግጭት ፤ ከቀውስ ፤ ከመፈናቀል፣ ከመጠራጠር ፤ ከጥላቻ ፤ ከበቀል ፤ ወዘተ . መታደግ አልቻለማ ፡፡እስኪ ለአንድ አፍታ ባህሎቻችንን እምነቶቻችንን ወይም ባህላዊ ንብረቶቻችንን ከዚህ አኳይ እንመዝነናቸው ፡፡ባክነዋል ወይስ በአግባቡ ስራ ላይ ውለዋል ! ?

አሁን ከምንገኝበት ሀገራዊ ቁመና አንጻር ባክነዋል ቢባል የሚያስኬድ ይሆናል፡፡ ታዲያ እነዚህን ባህላዊ ንብረቶቻችንን እንደ ጦር ዕቃ ለብሶ እንደ ጥሩር ደፍቶ መውጣት መግባት ፤ መመላለስ ለምን ተሳነን ! ? መልሱ ቀላል ነው ፡፡ላይ ላዩን እንከውናቸዋለን እንጅ አንኖራቸውም ፡፡

በቃል እናነበንባቸዋለን እንጂ በልባችን አላተምናቸውም ፡፡ ባልንጀራህን ፤ ጎረቤትህን እንደ ራሳህ ውደድ የሚሉ አብርሀማዊ እምነቶችን ማለትም ክርስትናን፣ እስልምናንና አይሁድን እየተከተልን እንዴት በጥል ግድግዳ ተለያየን ! ? በአንድ አምላክ በዋቄ ፈና እያመንን ኢ ሬቻን በየአመቱ እያከበርን እየከወን ይቅር መባባል ለምን ተሳነን !? መልሱን ለማግኘት ሚስጥሩን ለማወቅ ሞራ ማስገለጥ ወይም ኮከብ ማስቆጠር አያሻም ፡፡

መልሱ ቀላል ነው ፡፡እሱም ባህላዊ ንብረቶቻችንን በሳጥን ቆልፈን እንደ ክት ልብስ በየአመቱ በዓል ለማክበር ስለምናወጣቸው ነው ፡፡ እናከብራቸዋለን እንጂ አልከበርንባቸውም ፡፡ ስራ ላይ ስላላወልናቸው ( ኢንቨስት ) ስላላደረግናቸው ነው ፡፡ሀገራዊ ሰላምና አንድነት እውን ለማድረግ የተቆለፈባቸውን ባህላዊ ንብረቶች ከሳጥን አውጥቶ እያንዳንዱን ዜጋ በፍጥነት ማልበስን ይጠይቃል፡፡

እንደ ገና ስጦታ


ባህላዊ ወረታችን ቱባነቱን እንደጠበቀ ማደግ ዘመንና ትውልድ መዋጀት ይጠበቅበታል ፡፡አዎ! የትውልዱንና የዘመኑን ህፀፅ የሚያርም ለምፅ የሚያነጻ፣ የሚዋጅ መሆን አለበት ፡፡ ዘረኝነትን ፤ ጥላቻን ፤ ቂም በቀልን ፤ ደባን ፤ መከፋፈልን ፤ ወዘተ. መቤዥ ፤ መዋጀት አለበት ፡፡ባህላዊ ንብረታችንን ይበልጥ በማጎልበት ፤ በማልማትና በማስፋት ለመጻኢ እድላችን ፤ ለነገ ተስፋችን ፤ ለእርቅ ፤ ለሰላም ፤ ለአንድነት ፤ ለሁለንተናዊ ብልፅግና ፤ ወዘተረፈ ልናውለው ይገባል ፡፡

ስኬቶቻችንን የምናወድስበት ፤ ፈተናዎቻችንን የምንሻገርበት ነገአችንን የምንተልምበት ጭምር አድርጎ ስለመጠቀም አብክረን ማሰብ ያስፈልጋል ፡፡የፍቅር ፤ የእርቅ ፤ የሰላም ፤ የአብሮነት ፤ የማካፈል ፤ የመተባበር፣ የመተጋገዝ ፤ የመረዳዳት ፤ የምስጋና ፤ ወዘተረፈ . ባህሎች ፤ ልማዶች ፤ ዕምነቶች ፤ ሀይማኖቶች ከፍ ሲልም ድምር ባህላዊ ንብረቶች ባለቤት እንዲሁም የጥንታዊት ሀገር ባለቤት ሆነን አንድነትን በመከፋፈል ከሰዋን ፤ ፍቅር ከጎደለን ፤ እርቅ ከገፉን ፤ ሰላም ከራቀን፣ አብሮነትን በቀዬአዊነት ከተካን ፤ ማካፈልን በስስት ከቀየርን ፤ መተባበርን በመለያየት ከለወጥን፣ ምስጋናን በእርግማን ከተካን ፤ ወዘተረፈ . ምኑን ሙሉኡ ሆነው!? ፡፡

ባለፉት አራት አመታት ያለፍንባቸው ሀገራዊ ውጣ ውረዶች ፤ አሳፋሪ ድርጊቶች እውነት የእነዚህ ሁሉ መንፈሳዊና ባህላዊ ፀጋዎች ባለቤት ስለመሆናችን የሚመሰክሩ ናቸው !? በመሀላችን እየነገሰ ያለ ጥላቻ፣ ቂም በቀል ፤ ልዩነት ፤ ጎሰኝነት ፤ ወዘተረፈ. በእብነት ስንመለከት የደለበ ባህላዊ ወረቶች ባለቤት ካለው ሕዝብና ታሪክ የሚጠበቅ አይደለም ፡፡ ስለዚህ ብርሀን ልደቱን ከብርሀን ልደቱ ባሻገር ሌሎች ባህላዊ ወረቶቻችንም በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ልንኖራቸው ልንገልጣቸው ይገባል ፡፡

ሻሎም ! አሜን ፡፡

# ስፖርት



# ፔሌና ያልተነገሩ አስደናቂ ታሪኮቹ

**ቦጋለ አበበ**

ባለፈው ሳምንት በ82 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ፔሌ ባለፈው ረቡዕ ስርዓተ ቀብሩ ተፈፅሟል። በፈረንጆቹ 1940 በደቡብ ምሥራቅ ብራዚል ከድሃ ቤተሰብ የተወለደው ፔሌ፣ ድህነትን ለማሸነፍ ጫማ ከመጥረግ በዘለለ ብዙ ችግሮችን ተጋፍጣል። ችግሮቹን አሸንፎም በእግር ኳሱ የማይረሳ ታሪክ ጽፏል። በዚህም መላው ዓለም በእግር ኳስ ንጉሥነቱን እንዲቀበል አድርጋል። ኤዲሰን አራንቴስ ዶ ናሲሜንቶስ ወይም ፔሌ፣ ሦስት የዓለም ዋንጫዎች በማንሳት በታሪክ ብቸኛው ከመሆኑ በተጨማሪ በርካታ ግቦችንም በማስቆጠር የክብረወሰን ባለቤት ነው። ፔሌ የእግር ኳስ ነገር ሲነሳ ስሙ በቀዳሚነት የሚጠቀስ እና ታሪኩ ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት በመላው ዓለም የናኘ ሰው ቢሆንም ብዙ ያልተነገረ ታሪክና ገጠመኝ አለው። ከነዚህ መካከል ጥቂቶቹን በዛሬው የስፖርት ማህደር አምዳችን እንመልከት።

ጊዜው እኤአ 1968 ነው፣ የብራዚል ቡድን ለኦሊምፒክ ዝግጅት ይረዳው ዘንድ ከኮሎምቢያ አቻው ጋር የወዳጅነት ጨዋታ ለማድረግ ቦጎታ ነበር። በወቅቱ ቀይ ካርድ የሚባል ነገር የለም፣ የጨዋታው ዳኛ ጉሌርሞ ቬላስኬዝ ፔሌ በኮሎምቢያ ተጫዋች ላይ ጥፋት በመፈጸሙ ከሜዳ እንዲወጣ አዘዙ፣ በዚህ ጊዜ በስታዲየሙ ውስጥ ቀውጢ ተፈጠረ። ብራዚላውያኑ ተጫዋቾች የቡድናቸው ወሳኝ ተጫዋች ከሜዳ እንዲወጣ መታዘዙ አስቆጣቸው፣ የእግር ኳሱን ኮከብ ለመመልከት ስታዲየም የታደሙት ኮሎምቢያውያንም የፔሌን ከሜዳ መባረር በመቃወማቸው ግርግር ተፈጠረ። ዳኛውም በተፈጠረው ውዝግብ መሃል ጉሸማ ደርሶባቸው ፊሽካቸውን ለአንደኛው የመስመር ዳኛ አስረክበው ከሜዳ ሲወጡ፣ ፔሌ ወደ ጨዋታው እንዲመለስ ተደርጎ ግጥሚያው የቀጠለበት አጋጣሚ ፔሌ ምን ያህል ተፅዕኖ እንደነበረውና በሁሉም ዘንድ እንደሚወደድ ያሳየ ነው።

ሌላው ፔሌ ሲነሳ ጨዋታ ለማየት ተኩስ አቁም የተደረገበት አስደናቂ አጋጣሚ ነው። እኤአ በ1960ዎቹ ፔሌ የሚጫወትበት የሳንቶስ ቡድን በዓለም ላይ ካሉ ዝነኛ ክለቦች መካከል አንዱ በመሆኑ፣ ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስገኙ የወዳጅነት ጨዋታዎችን በዓለም ዙሪያ እየተጓዘ ያደርግ ነበር። ከእነዚህ ጨዋታዎች መካከል ሳንቶስ በ1969 በእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ወደ ነበረችው አፍሪካዊት አገር ናይጄሪያ በመሄድ በቤኒን ከተማ ካለ ቡድን ጋር ተጋጥመው 2 ለ 1 አሸንፏል።

በወቅቱ ቢያፍራ የተባለችውን ግዛት ከናይጄሪያ ለመገንጠል የተጀመረ ጦርነት ይካሄድ ነበር። ፔሌ የሚገኝበት የሳንቶስ ቡድን የደኅንነት ስጋት ስለነበረው ለጨዋታ ከማምራቱ በፊት ተዋጊዎቹ ወገኖች ተኩስ ለማቆም ተስማምተው ነበር።

በእርስ በርስ ጦርነቱ የሚሳተፉት ወገኖች ጨዋታው በሚካሄድበት ወቅት ጦርነቱን እንደሚያቆሙ እና አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ጥቃት እንደማይሰነዝሩ አረጋግጠዋል።ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ዝነኛው ፔሌ በቡድኑ ውስጥ መካተቱ ነበር።

የሳንቶስ ቡድን ተጫዋቾች እኤአ በ1972 ለግጥሚያ ወደ ካሪቢያኗ አገር ትሪንዳድ ኤንድ ቶቤጎ ለግጥሚያ በሄዱበት ጊዜ በአገሪቱ ሰላም ስላልነበረ በቶሎ ግጥሚያቸውን አደርገው ወደ አገራቸው ለመመለስ ጓጉተው ነበር። ነገር ግን በጨዋታው ላይ በ43ኛው ደቂቃ ፔሌ ግብ ሲያስቆጥር ያልጠበቁት ነገር ተከሰተ። በስታዲየሙ የነበሩት ተመልካቾች በደስታ ሜዳውን ጥሰው ገቡ። ከዚያም ግብ ያስቆጠረውን ፔሌን በትከሻቸው ላይ ተሸክመው ከስታዲየም ውጪ ይዘውት በመውጣት በጎዳናዎች ላይ እየጨፈሩ ደስታቸውን ይገልጹ ነበር።



በወቅቱ ከቡድኑ አባላት ተለይቶ በደጋፊዎቹ ወደ ጎዳና የተወሰደውን ፔሌን ከትከሻቸው ላይ አውርዶ ከቡድኑ ጋር ለመቀላቀል ከፍ ያለ ጥረት ተደርጋል።

ፔሌ ድንቅ አጥቂ ብቻ አልነበረም፣ በተቃራኒው ግብ ጠባቂ ሆኖ በተጫወተበት አጋጣሚ አንድም ጊዜ ግብ አለማስተናገዱ ብዙዎችን ያስገርማል። ፔሌ ቡድኑ ሳንቶስ በተጫወተባቸው ዓመታት አራት ጊዜ ግብጠባቂ ሆኖ የመሰለፍ እድል ገጥሞታል። አንደኛው ቡድኑ ለብራዚል ቻምፒዮና ለግምሽ ፍጻሜ በደረሰበት ወቅት ነበር። ፔሌ በግብ ጠባቂነት በተሰለፈባቸው ጨዋታዎች ላይ አንድም ግብ ተቆጥሮበት አያውቅም።

ፔሌ በተነሳ ቁጥር የሚታወስ አንድ ታሪክ አለ። ይህ ታሪክ ከኢትዮጵያው የስፖርት አባት ይድነቃቸው ተሰማ ጋር የተያያዘ ነው። እኤአ በ1970 13ኛው የዓለም ዋንጫ በሜክሲኮ እየተካሄደ ነበር። ዓለም ዋንጫውን አስመልክቶ ለኢትዮጵያውያን ትንታኔ ያቀረቡት ይድነቃቸው ተሰማ ሲሆኑ ጥያቄያቸውን ለማቅረብ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን በሚሰራጭ ፕሮግራም ላይ 10 የስፖርት ጋዜጠኞች ተገኝተዋል። ደምሴ ዳምጤ ከኢትዮጵያ ሬድዮ፤ ግርማ ሰይፉ ከአዲስ ዘመን፤ በሃይሉ አስፋው ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ ኢብራሂም ሃጂ ከበሪሳ ጋዜጣ፤ ሰለሞን ገብረእግዚአብሔር ከኢቲቪ፤ ይንበርብሩ ምትኬ ከኢትዮጵያ ሬድዮ፤ ሃድጉም መስፍን ከዓልአለም ጋዜጣ፤ ገዛህኝ ፂዮን መስቀል ከኢዜአ እና አዋያዩ ፀጋ ቁምላቸው ነበሩ።

90 ደቂቃዎችን በፈጀው መግለጫ ላይ ላይ ከቀረቡ ጥያቄዎች አንዱ ከፔሌና ከማራዶና የቱን ያደንቃሉ? የሚል ነበር። ይድነቃቸው ምላሽ ሲሰጡ "አንድ ያልገባችሁ ነገር ፔሌን አናውቀውም ስትሉ እራሳችሁን ልጅ ማድረጋችሁ ነው? ወጣት ነኝ ለማለት ካልፈለጋችሁ በቀር ፔሌ ሲጫወት አይታችሁታል። ማራዶና በአሁኑ ትውልድም እንደምናየው ጥሩ ተጫዋች ነው ግን ግራኝ ነው" ብለው ማስረዳታቸውን ሲቀጥሉ ሁለቱን ተጨዋቾች ማነፃፀር በእጅጉ እንደሚከብድ ሊያመለክቱም ሞክረዋል። ፔሌ በሁለቱም እግሮቹ እንደሚጫወት፤ ሰውነቱም የተደላደለ እንደሆነና ኳስን የመቆጣጠር ብቃቱ በጣም የተሻለ መሆኑን ይድነቃቸው አስረድተዋል። ማራዶና ብዙ ጊዜ ኳስን በእራሱ እንደማይነካ ፔሌ በአንፃሩ ብዙ ጎሎችን ያስገባው በጭንቅላቱ ገጭቶ እንደሆነና ፍጥነቱም እንደሚያስደንቅ አብራርተዋል። ማራዶና ሰባት የእንግሊዝ ተጫዋቾችን አብዶ ሰርቶ ማግባቱ አለምን ማስደነቁን የጠቀሱት ይድነቃቸው፤ ፔሌ እስከ ዘጠኝ ተጫዋቾችን አብዶ ሰርቶ ማግባቱን ይህን ብቃቱንም ከ30 ጊዜ በላይ እንደደገመው አስቀምጠዋል።




# በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ

**በስጥሻቸው ልውልሰገድ**

ሰላም ልጆች እንዴት ሰነበታችሁ፤ ሳምንቱ እንዴት አለፈ? በጣም ቆንጆ ነበር እንዳላችሁኝ እርግጠኛ ነኝ፤ምክንያቱም ይህ ሳምንት በኢትዮጵያ በደማቅ ሁኔታ የሚከበረው የገና በዓል የተከበረበት ነው። ልጆች በዓል እንዴት ነበር? እኔጋ በጣም ቆንጆ ነበር። በአል ሲመጣ እንኳን አደረሳችሁ መባባል ባህላችን ነውና እንኳን ለእየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ።

ዛሬ ይዤላችሁ የቀረብኩት የገና በዓል ላይ ያተኮረ ፅሁፍ ነው። ልጆች የገና በዓል በሁለት መንገድ ይከበራል። አንደኛው ከእምነት አንፃር ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከባህል አንፃር ነው። በመጀመሪያ ከእምነት አንፃር እንመልከት፤ የክርስትና እምነት ተከታዮች የገና በልን የልደት በዓል ወይም የውልደት በዓል በማለት ይጠሩታል። ይህ በዓል የእየሱስ ክርስቶስን በከብቶች በረት መወለድ የሚዘከሩበት ነው።

በንጉስ አውግስቶስ ቄሳር ዘመን ንጉሱ ሰው ሁሉ እንዲቆጠር ባዘዙ ጊዜ፤ ሰው ሁሉ ለመቆጠር ወደየትውልድ ቦታው መሄድ ጀመረ። ዮሴፍ እና የእየሱስ ክርስቶስ እናት ማርያምም ሊቆጠሩ ከናዝሬት ወደ ቤቴልሄም ጉዞ አደረጉ። በቤቴልሄም ሳሉም ማርያም የምትወልድበት ጊዜ ደረሰ፤ በቦታው ብዙ እንግዳ ነበርና የምታርፍበት ቦታ አልነበረም በመሆኑም ማደሪያ ስላልነበራቸው በከብቶች በረት ውስጥ ልጇን እየሱስ ክርስቶስን ወለደችው።

በዚያን ሌሊት ከብት ሲጠብቁ የነበሩ እረኞች ህፃን ልጅ በጨርቅ ተጠቅልሎ በከብቶች በረት ውስጥ ተኝቶ ባዩት ጊዜ እጅግ ተደሰቱ። ደስታቸውንም "በሰማይ ለእግዚያብሄር ክብር ሆነ በምድርም ለሰው ልጆች በጎ ፍቃድ ሆነ" በማለት ገለፁ። እንግዲህ ልጆች ይህ የገና በዓል ከእምነት አንፃር የሚከበርበት ምክኒያት ነው።



ሌላኛው ደግሞ ከባህል አንፃር የሚከበርበት ነው።በኢትዮጵያ የገና በዓል ሲከበር ዘመድ አዝማድ እየተገናኘ እንኳን አደረሰህ? እንደምን ከረምክ ?ልጆች፤ አዝመራው፤ እህሉ ፤ጤንነት እንዴት ነው? የሚባባልበት በዓል ነው። በዓል ሲቃረብ ለበዓሉ የሚሆን ጠላ ይጠመቃል፣ በዋዜማው ድፎ ዳቦ ይጋገራል ከዚያም ሲል ደግሞ ጠጅ ይጣላል።

ልጆች መቼስ "በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ "፣ "በገና ጨዋታ የለም ሎሌ ጌታ" ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ ብዬ አስባለው። እንደዚህ የሚባለው ለምን እንደሆን ታውቃላችሁ? በገና በዓል ሁሉም ሰው እኩል የመደሰት መብት ይሰጠዋል። በዓሉን አስመልክቶ የሚደረግ ‹‹የገና ጨዋታ›› በመባል የሚታወቅ ባህልዊ ጨዋታ በወንዶች መካከል ይካሄዳል። በዚህ ጨዋታ ላይ ማንም ከማንም ልዩነት ሳይደረግበት እኩል ይሳተፋል። በተለይ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እረኞችም ሆኑ አለቆቻቸው የገና በዓል ቀን እኩል በጨዋታው ይሳተፋሉ፤ በዚያን ቀን አዛዥና ታዛዥ አለቃና ሰራተኛ የሚባል ነገር የለም ። በፍቅርና በነፃነት አበረው በዓሉን ያከብራሉ።

የገና ጨዋታ የገና በዓልን መድረስን ተናፋቂ ከሚያደርጉ ነገሮች ውስጥ ዋናውና የበዓሉም ድምቀት ነው። ልጆች የገና ጨዋታ መቼ እንደተጀመረ የሚገልፅ ትክክለኛ መረጃ ባይኖርም ከክርስቶስ ልደት በፊት እረኞች በተለይ በበጋው ወቅት ከብት እየጠበቁ መስክ ላይ የጫወቱ እንደነበር ይነገራል። ታዲያ ልጆች የገና ጨዋታን ለመጫወት ሩር እየተባለ የሚጠራ ድቡልቡል ያስፈልጋል። ክብደቷ እስከ አምስት መቶ ግራም የሚመዝን ከእንጨት፤ ከጠፍር አሁን አሁን ደግሞ ከፕላስቲክ ይዘጋጃል። ድቡልቡል መጫወቻ ወይም ሩሩን ለመምታትና ወደ ተቃራኒ ቡድን ግብ ለማስቆጠር ልክ እንደማንኪያ ቅርፅ ያለው ከአንድ ሜትር የማይበልጥ ቁመት ያለው የገና ዱላ ያስፈልጋል።

እንግዲህ ልጆች የገና ጨዋታ ላይ ተንኮል የለም፤ ሁሉም በፍቅር ከልብ ይጫወታል፤ ማንም አውቆ ሌላን ሰው አይጎዳም። ይህ የገና ጨዋታ የሚደረገው ኢትዮጵያ ብቻ ውስጥ ነው፤ ይህም የሚያሳየው ሀገራችን ምን ያህል የሚያምር የራሷ የሆነ ባህል እና የባህል ማድመቂያ የሆኑ ጨዋታዎች እንዳሏት ነው። እናንተም እነዚህን ባህሎችና የበዓል ጨዋታዎች ማወቅ አለባችሁ፤ ጎበዝ ልጆች የራሳቸውን ባህል፣ ቋንቋና ወግ ጠንቅቀው ያውቃሉ እናንተ ደግሞ ጎበዞች ስለሆናችሁ ቤተሰቦቻችሁን ስለሀገራችሁ ባህል ጠይቃችሁ ማወቅ ይኖርባቹሃል።

ልጆችዬ ብዙ ጊዜ የገና በዓል ሲመጣ አብዛኞቻችን የምናስታውሰው የገና ዛፍ ማዘጋጀትና በተለያዩ ጌጣጌጦች ማሳመር ነው፤ ነገር ግን ይህ የኛ ባህል አይደለም። ይህ ባህል የፈረንጆች ባህል ነው በዚያ ላይ ደግሞ ከጥቅሙ ጉዳቱ እጅግ ያመዝናል፤ ምክኒያቱም የገና ዛፍ ለማዘጋጀት የግድ ዛፍ መቁረጥ አለብን የህ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የእፅዋት ጭፍጨፋን ያስከትላል።

ልጆች ትምህርት ቤት ስለእፅዋት ስትማሩ የእፅዋት መመናመን የሚያስከትለውን የአየር መዛባት ትማራላችሁ፤ በትምህርታችሁ ታዲያ የደን መመናመን ከፍተኛ የሆነ የሙቀት መጨመርን እንደሚያሥከትል መምህራኖቻችሁ ያስተማሯችሁን ታስታውሳላችሁ ብዬ አስባለው። ስለዚህ ለገና በዓል ብለን ዛፍ መቁረጥ ምን ያህል ጉዳት እንደሚያስከትል አውቀን ይህንን ባህል በራሳችን ሃገርኛ ባህል መተካት አለብን ማለት ነው።

እናንተም ለገና ብላችሁ ጥድ ዛፍ መቁረጥ የለባችሁም ከዚያ ይልቅ በጣም ደስ የሚለውን የገና ጨዋታ ከእድሜ እኩዮቻችሁ ጋር በመጫወት ማክበር ትችላላችሁ። በሚቀጥለው አመት እንደዚህ ባለ መልኩ እንደምታከብሩ ተስፋ አደርጋለሁ። በሉ ልጆች የዛሬ ፅሁፌን እዚህ ላይ ላብቃ ፤ሳምንት በሌላ ፅሁፍ እስክንገናኝ መልካም የበዓል ሳምንት ይሁንላችሁ።